# የፌደራል የፍትህ አካላት ባለሙያዎች

# ስልጠና ማዕከል

**ለቅድመ ስራ ስልጠና ሰልጣኞች የተዘጋጀ**
**የስልጠና ሞጁል**

## የገጠር መሬትን የሚመለከቱ ህጎችና አፈጻጸም

በፌደራል የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ስልጠና ማእከል የተዘጋጀ

## Contents


መግቢያ ........ 3

ምዕራፍ አንድ ........ 6

ስለ መሬት ባለቤትነትና የመሬት ሥፋት በጠቅላላው ........ 6

1.1. የመሬት ባለቤትነት የመሬት ሥሪትና አጠቃቀም በዘውዳዊው ሥርዓት ........ 7

11.1. የመንግስት ሀብትና ንብረት ስለሆነ መሬት ........ 7

1.1.2. የእርስት ፣ የጉልት፣ የዕርስት ጉልትና የገባር የመሬት ሥሪት ........ 8

1.2. የመሬት ባለቤትነት የመሬት ይዞታና አጠቃቀም በደርግ ሥርዓት ........ 12

1.3. የመሬት ባይዞታነትና የመጠቀም መብት በሽግግር ወቅት ........ 15

ምዕራፍ ሁለት ........ 17

የመሬት ባለይዞታ የመሆንና የመጠቀም መብት በኢፌዲሪ ህገ መንግስት ........ 17

ምዕራፍ ሦስት ........ 25

መሬት በነፃ የማግኘት ይዞታና መሬትን የመጠቀም መብት በክልል የህግ ማዕቀፎች ........ 25

ምዕራፍ አራት ........ 39

የፌደራሉንና የክልሉን የህገ ማዕቀፎች በማስፈፀም በኩል የሚታዩ ችግሮች የመፍትሔ ሀሳቦች ........ 39

4.1 በአርሶ አደሮች መካከል መሬትን መነሻ ያደረጉ ክርክሮች በሚመለከት፣ ........ 39

4.3. የመፍትሔ ሀሳቦችና ማጠቃለያ ........ 46

## መግቢያ

ኢትዮጵያ ባለፈችባቸው የረዥም ጊዜ የታሪክ ዘመናት የአገሪቱ ፖለቲካል ኢኮኖሚ መሠረታዊ አጀንዳ ሆኖ የቆየና አሁንም ቁልፍ የፖለቲካ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የመወያያ አጀንዳ ሆኖ የሚገኘው የመሬት ባለቤትነት የመሬት ይዞታ እና የመሬትን አጠቃቀም ጉዳይ ነው፡፡

ቀድሞ የነበረው የመሬት ይዞታ ስሪት እና ባለቤትነት ብዙሀኑን የአገሪቱን አርሶ አደሮች ለጥቂት ባለቤቶችና የገዥው መደብ አባላት ጭሰኝነትና ባርነት የዳረጉበት መሣሪያ የነበረ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ የአፄው ሥርዓትና ይከተለው የነበረው የመሬት ባለቤትነት ስሪት ሰፊው አርሶ አደርና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች “መሬት ላራሹ” የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ በማንገብ ባደረጉት ረዥምና መራራ ትግል ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተወግዷል፡፡ ህዝቡ ከዳር እስከዳር በአፄው ሥርዓት ላይ ህዝባዊ ቁጣ በመግለፅ ያደረገውን ትግል ውጤት በአቋራጭ ነጥቆ የነበረው ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ በከተማና በገጠር የሚገኝ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ሙሉ በሙሉ በአዋጅ በመውረስ የመንግስትና የህዝብ ንብረት መሆኑን በይፋ አውጇል፡፡ ህጉንም ለማስፈፀም የተለያዩ ተግባራዊ እርምጃዎችን ወስዷል፡፡

ሆኖም የደርግ መንግስት የእርሻ መሬትን ለአርሶ አደሩ ለማከፋፈል የወሰዳቸው የተለያዩ እርምጃዎች፣

- የአርሶ አደሩን የባለይዞታነትና መሬቱን በዘላቂነት የማልማትና የመጠቀም መብት ዋስትና እና ጥበቃ በማይሰጥ ሁኔታ ተደጋጋሚ የሆነ የእርሻ መሬት ክፍያ ያደረገ መሆኑ፣
- የአርሶ አደሩን ምርቱን የመሸጥና የመጠቀም መብት የሚጋፋ የኮታ የምርት ሽያጭ አሠራር ይከተል የነበረ በመሆኑ፣

አርሶ አደሩ የእርሻ ማሳውን የማልማት ፍላጎት ያጎደለና ምርታማነትን የቀነሰና የአፄው ሥርዓት ሲወድቅ ህዝቡ የነበረውን ተስፋ ዕውን ማድረግ ያልቻለ መሆኑን በዚህ መስክ በየጊዜው የተደረጉ ጥናቶች ያረጋግጣሉ፡፡

የደርግ መንግስት በህዝብ መራራ ትግል ከተወገደ በኋላ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት የመንግስትና የኢትዮጵያ ብሄርብሄረሰቦችና ህዝቦች ባለቤትነት ሥር ሆኖ የሚቆይ ስለመሆኑ ግልፅና የማያሻማ አቋም ተይዞበታል፡፡ መንግስት በአንድ በኩል መተኪያ የሌለውን ይህንን የአገሪቱን ሀብት ልማቱን ለማፋጠንና የአርሶ አደሩንና አርብቶ አደሩን የመሬት ባለይዞታ የመሆንና የመጠቀም መብት ህገ መንግስታዊ ዋስትና በመስጠትና የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የህግ ማዕቀፎች በፌዴራልና በክልል መንግስታት በኩል በማወጅ እንዲሁም የገጠር ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ በመቅረፅና ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ ሰፊ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

በኢፌዲሪና በክልል ህገ መንግስቶች እንዲሁም በፌዴራልና በክልል መንግስታት በወጡ የህግ ማዕቀፎች መሰረት ለአርሶ አደሩና ለአርብቶ አደሩ መሬት በነፃ የማግኘትና የመሬት ባለይዞታ የመሆንና መሬቱን የመጠቀም መብት ተግባራዊ በማድረግ ሂደት በየአካባቢው የሚከሰቱ የተለያዩ ችግሮች እንዳሉና እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍና ህገ መንግስቱንና የህግ ማዕቀፎችን መሠረት በማድረግ ተገቢውን ውሳኔ በመስጠት በኩል የፍትህ አካላት የማይተካ ድርሻ ያላቸው መሆኑ ግልፅ ነው፡፡

ሆኖም ህገመንግስቱን ድንጋጌና የህግ ማዕቀፎቹን መሠረታዊ ግብና ዓላማ በመረዳት ህጎቹን በመተርጎምና በማስፈፀም በኩል የፍትህ አካላት በኩል ቀላል የማይባል የግንዛቤ፣ የክህሎትና የአመለካከት ችግሮች ምክንያት አርሶ አደሮች የምርት ሥራቸውን በመተው በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች ጊዜቸውን በክርክርና በሙግት ከማህበራዊ ፍርድ ቤት እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሚከራከሩበት ሁኔታ እንዳለ በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች የሚከፈቱ መዛግብት ብዛት በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

ስለሆነም የአርሶ አደሩንና የአርብቶ አደሩን የመሬት ባለይዞታ የመሆንና መሬትን የመጠቀም መብት ለማረጋገጥ የተደነገጉትን የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎችና በፌዴራልና በክልል የህግ ማዕቀፎች መሠረታዊ ግብና ይዞታ ህጉን በማስፈፀምና በመተርጎም በኩል የሚታዩ ችግሮች የችግሮቹን መንስኤና ችግሮቹን ለመፍታት የሚያስችል የመፍትሄ ሀሳቦች ላይ በጋራ በመወያየት የጋራ ግንዛቤ በመያዝ በአመለካከትና በክህሎት ረገድ የሚታዩ ችግሮችን ማስወገድ ዓላማው ያደረገ ይህ የስልጠና ጽሁፍ ተዘጋጅቷል፡፡

ይህ ፅሁፍ በገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም በኩል የሚታዩ ችግሮችን የችግሮቹን መንስኤና የመፍትሄ ሀሳቦችን በተሟላ ሁኔታ ለመዘርዘር ታስቦ የተዘጋጀ አይደለም፡፡ የፅሁፍ ዓላማ ለውይይት መነሻ የሚሆኑ መሠረታዊ ነጥቦችን በማቅረብ ሠልጣኞች በየአካባቢያቸው ያለውን ችግር የችግሩን መንስኤና ችግሩ ሊፈታ ስለሚችሉበት ሁኔታ ያላቸውን ዕውቀትና ልምድ ተለዋውጠው የጋራ ግንዛቤ እንዲይዙ ለማነሳሳት መሆኑን በመገንዘብ ሠልጣኞች ንቁ ተሣትፎ በማድረግ ፅሁፉን ለማዳበር ለማሻሻልና ለማስተካከል የሚረዳ ተሞክሮችን እንዲያቀርቡ ይጠበቃል፡፡

## የሥልጠናው ዓላማዎች

በስራ ላይ ስልጠና ተሳታፊ የሆኑ ባለሙያዎች ስልጠናውን ሲጨርሱ፣

1. በዘውዳዊው ስርአት ስለነበረው የመሬት ስሪትና አጠቃቀም እንዲሁም ስላስከተላቸው ችግሮች ማብራራት ይችላሉ፡፡
2. በደርግ ስርአት ስለነበረው የመሬት ስሪትና አጠቃቀም እንዲሁም ስላስከተላቸው ችግሮች ማብራራት ይችላሉ፡፡
3. በኢፌዲሪ ህገመንግስት መሬትን በተመለከተ የተደነገጉት ድንጋጌዎችን መግለጽና ማብራራት ይችላሉ፡፡
4. በፌዴራል መንግስት የገጠር መሬት አጠቃቀምን በተመለከተ በሁሉም ክልሎች ተፈጻሚ የሚሆኑ አስገዳጅ መርሆዎችና ድንጋጌዎችን አውቀው ማስረዳት ይችላሉ፡፡
5. በዚህ ሞጁል በዝርዝር በቀረቡት በኦሮሚያ፣ ትግራይ፣ አማራ እና ደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልሎች፣
    - የገጠር መሬት በነጻ የማግኘት መብት ስላላቸው ሰዎች፣
    - የገጠር መሬትን በስጦታና በውርስ ስለማስተላለፍ በየክልሉ ባሉት ህጎች መካከል ስላሉት አንድቶችና ልዩነቶች፣
    - የገጠር መሬት ባለይዞታዎች የመጠቀም መብታቸውን ማከራየት በተመለከተ ስላሉት ድንጋጌዎች አንድነትና ልዩነት፣
    - በገጠር መሬት ላይ የተፈሩ ቋሚ ተክሎችና ሀብቶችን በሚመለከት የባለይዞታዎች መብትን በተመለከተ ስላለው አንድነትና ልዩነት፣

- በመሬት ይዞታ መጠቀም ቀሪ ስለሚሆንባቸው ሁኔታዎች በየክልሉ ህጎች መካከል ስላለው አንድነትና ልዩነት፣
- ከመሬት ይዞታና መጠቀም መብቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱ አለመግባባቶች ስለሚፈቱበት ስርአት በየክልል ህጎቹ መካከል ስላለው አንድነትና ልዩነት፣
- የመሬት ሽግሽግን በተመለከተ በየክልሉ ህጎች መካከል ስላለው አንድነትና ልዩነት፣

ማስረዳትና ማብራራት ይችላሉ፡፡

6. ከገጠር መሬት ይዞታ ጋር በተያያዘ በፍርድ ቤት ስለሚያጋጥሙ ችግሮችና መፍትሄዎች በቂ ግንዛቤ በማግኘት በህጉ መሰረት መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችል እውቀትና ክህሎት ይኖራቸዋል፡፡

## ምዕራፍ አንድ

## ስለ መሬት ባለቤትነትና የመሬት ሥሩት በጠቅላላው

መሬትና በአገሪቱ ግዛት ክልል የሚገኙ የውሀ አካሎች እና በገፀ ምድርና ከርሰ ምድር ውስጥ የሚገኙ ሀብት የባለቤትነትና የአጠቃቀም ሁኔታ አገሮች በህገ መንግስታቸውና በሌሎች ህጎች ምላሽ የሚሰጡት ቁልፍ ጉዳይና የአንዲት አገር ኢኮኖሚካል ሉዓላዊነት ማረጋገጫ ዋነኛ መንገድ ነው፡፡ የመሬት ባለቤትነት የመሬት ሥሪትና የመሬት አጠቃቀም በተመለከተ የዘውዳዊ ሥርዓት መንግስት፣ የደርግ መንግስት፣ የሽግግር ወቅት መንግስትና የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በተለያየ መንገድና መልክ የሚገለጽ የፖሊስ አቅጣጫዎችን የሚከተሉ ስለመሆኑ በየወቅቱ የወጡ የህግ ማዕቀፎችን የመንግስት ውሣኔዎችንና በልምድ የዳበሩ አሠራሮችን በመመርመር ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም የመሬት ባለይዞታነትና ባለቤትነትን፣ የመሬት ስሪትና የመሬት ባለይዞታነትና አጠቃቀምን በተመለከተ በተለያየ ጊዜ አገሪቱ ስትከተለው የነበረውን መሠረታዊ የፖሊሲ ሀሳብና አሠራር ለመረዳት ይቻል ዘንድ የዘውዳዊ ሥርዓት ደርግና የኢፌዲሪ መንግስት ይከተሉት የነበረውን

የፖሊስ ሀሳብና ተግባራዊ ያደርጉት የነበረውን አሠራር በማነፃፀር በአጭሩ ማየት አስፈላጊ ነው፡፡

## 1.1. የመሬት ባለቤትነት የመሬት ሥሪትና አጠቃቀም በዘውዳዊው ሥርዓት

የመሬት ባለቤትነትና የመሬት ሥሪትን አስመልክቶ አንድና ወጥ የሆነና በህግ የተደነገገ አሠራር በአፄው ሥርዓት አልነበረም፡፡ ኢትዮጵያ በተለያዩ ንጉሠ ነገስቶችና ንጉሶች በምትተዳደርበት ወቅት በስሜኑና በአገሪቱ መካከለኛ ክፍል የነበረው የመሬት ሥሪት ግዛትን ለማስፋፋት ነገስታቱ ባደረጉት ወረራ እና ጦርነት ከያዙት የአገሪቱ ደቡብ፣ ደቡብ ምሥራቅና የደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች ይሠራበት ከነበረው የመሬት ሥሪት በእጅጉ የተለየ ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አገሪቱ ከሌሎች አገሮች ጋር በምትዋሰንባቸው ቆላማና ጠረፍ አካባቢዎች ማዕከላዊ መንግስት የሚያውቀውና የሚያስፈፅመው ግልፅ የሆነ የመሬት ባለቤትነትና ሥሪት አልነበረም፡፡ በአጠቃላይ አገሪቱ በንጉሣዊ አገዛዝ በነበረችበት ወቅም በተግባር ላይ ይውል የነበረው የመሬት ባለቤትነትና ሥሪት ወጥነት የሌለውና የተለያየ መንገድ ሊገለፅ የሚችል ነው፡፡ ይኸውም

- የመንግስት ሀብትና ንብረት የሆነ መሬት
- የቤተሰብና የግለሰቦች ሀብትና ንብረት የሆነ መሬት
- የመሬቱ ንብረትነቱ የመንግስት ሆኖ መሬቱን የመጠቀምና አላባ የመሰብሰብ መብት የግለሰቦች የሆነ መሬት ሥሪት በማለት ከፋፍለን ለማየት እንችላለን፡፡

### 11.1. የመንግስት ሀብትና ንብረት ስለሆነ መሬት

በመጨረሻው አፄ ሥርዓት በመሬት ውስጥና ከሁሉም ውኃ በታች ያለው ሀብት በሙሉ የመንግስት ንብረት መሆኑ 1948 ዓ.ም በተሻሻለው ህገ መንግስት አንቀፅ 130 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመረምረው የመሬቱ ባለሀብትነት የግለሰብ የቤተሰብ ወይም የማህበረሰብና የመንግስት መሆኑ ልዩነት ሣይደረግ በከርሰ ምድር ውስጥ የሚገኝ ማናቸውም ሀብት የመንግስት ንብረት መሆኑና በወንዞች በሀይቅ ወይም በማናቸውም ውኃ ሥር የሚገኝ የተፈጥሮ ሀብት በመንግስት ባለቤትነት ንብረት የነበረ መሆኑን የህገ መንግስቱን አንቀፅ 130 ድንጋጌዎች በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

የገፀ ምድርና በውሀ የተሸፈኑ መሬትን ባለቤትነት አስመልክቶ መንግስት በማናቸውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የኢትዮጵያ ዜግነት በተሰጠው ማህበር ያልተያዘ መሬት፣ ህጋዊ ባለቤት ባለመኖሩ የተለቀቀ ዕርስት፣ የአፈር፣ የጫካ፣ የግጦሽ መሬት፣ ባህሮችና ወንዞች ጠረፎች እና አየሩ ጭምር መንግስት ባለቤት እንደሆነ ይደነግጋል፡፡

በዚህ ድንጋጌ መሠረት ባለቤት የሌለው ጠረፍ መሬት ደንና ወንዞች ሀይቆችና ማናቸውም በውሀ የተሸፈነ መሬት በጠረፍ አካባቢ የሚገኝ በስፋት አርብቶ አደሮች ከሥፍራ ወደ ሥፍራ እየተዘዋወሩ ከብት እያረቡ የሚኖሩባት ቦታ ሁሉ የመንግስት ንብረት እንደሆነና መንግስት ይህንን ንብረት ለመጠበቅ የሚያስችል አሠራር የመዘርጋት ኃላፊነት እንዳለበት 1948 ዓ.ም የተሻሻለው ህገ መንግስት በግልፅ የደገነነ መሆኑን ለመረዳት እንችላለን፡፡

## 1.1.2. <u>የእርስት ፣ የጉልት፣ የዕርስት ጉልትና የገባር የመሬት ሥሪት</u>

### ሀ/ <u>የርስት የመሬት ሥሪት</u>

የዕርስ መሬት በሰሜንና መካከለኛው የአገሪቱ ክፍል የነበረ አሠራር ሲሆን መሬት በቤተሰብ ሀብትና ንብረትነት የተያዘና ማናቸውም የዘር ሀረጉ ዕርስት ለማካፈል የሚያስችለው ሰው የስር ዘር አረጉን መዝዞ በዕርስት የተያዘውን መሬት የሚካፈልበት፣ የሌሎቹን ዕርስት ተካፋዬች ፍቃድና ስምምነት ሳያገኝ ተካፍሎ የያዘውን መሬት ከመጠቀም ውጭ ለመሸጥ ወይም በወለድ አገድ ለማስያዝ የማይችልበት የመሬት ሥሪት እንደነበር በዚህ መስክ የተደረጉ ጥናቶች ያሣያሉ፡፡

ይኸ የመሬት ሥሪት “የዕርስት” የመሬት ሥሪት ተብሎ የሚጠራ ሲሆን የመሬት ባለ እርስት የሆነ ሰው ንጉሱ ለሚጠራው ዘመቻ ለመዝመት ሁል ጊዜ ዝግጁ ሆኖ የመጠበቅ፣ ለዘመቻ ሲጠራ ሳያቅማማ ግዳጁን መወጣት፣ በየደረጃው ላሉ ሹሞች መማለጃና ዳረጎት የመክፈል ግዴታ የነበረበት፣ “ባለዕርስቱ” እነዚህን ግዳጆች በአግባቡ ካልተወጣ ከዕርስቱ የሚነቀልበትና መሬቱ ለሌላው ዕርስት ተካፋይ ወይም ለሌላ ሰው ይሰጥበት እንደነበርና ይኸ ዘዴ ነገስታቱ በአገሪቱ ሰሜንና መካከለኛ ክፍል ይኖር የነበረውን አርሶ አደር የሚያዙትን ማናቸውም ግዳጅ ፈፃሚ ሆኖ በታማኝነት እንዲሰለፍና እንዲገዛ ለማድረግ ያስቻላቸው መሆኑን በዚህ ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች ያረጋጣሉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ሥርዓቱ ዕርስት የሌላቸው ገበሬዎች ባለዕርስት ለሆኑ ሰዎች በጭሰኝነት እያረሱ የጉልበታቸውንና የድካማቸውን ፍሬ ሙሉ በሙሉ የሚያስረክቡና በርካታ አርሶ አደሮችን ለግፍና ለረገጣ የዳረገ የመሬት ሥሪት እንደነበር በዚህ ዙሪያ የተፃፉ ፅሁፎች ያረጋግጣሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የዕርስ ተካፋይ ነኝ አይደለህም ተገቢው ድርሻ አልተሰጠኝም ተሰጥቶሀል በሚሉና በሌሎች ምክንያቶች አርሶ አደሩን ከአጥቢያ ዳኛ ጀምሮ እስከ ዙፋን ችሎት ድረስ አላግባብ እንዲሟገት ጥሪቱን እንዲያሟጥጥ ለእንግልት ለፍትህ እጦት እንዲጋለጥ የዳረገ የመሬት ሥሪት የነበረ መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 31/67 አንቀፅ 28 መሠረት የተቋረጡ የመሬት ክርክርና ሙግት ይደረግባቸው የነበሩ መዛግብትን ቁጥርና እድሜ በማገናዘብ ለመረዳት እንደሚቻል በመስኩ በተደረገ ጥናት ተረጋግጧል፡፡

## ለ/ <u>የጉልት ገዥ የመሬት ሥሪት</u>

የጉልት የመሬት ሥሪት በአፄ ሚኒሊክ ጊዜ በተደረገው ወታደራዊ ወረራ ወደ ደቡብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ምስራቅና ደቡብ ምሥራቅ የዘመቱ ወታደሮች በየአካባቢው የሚኖሩ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች በልማዳዊ ህግ መሠረት በባለቤትነት ይዘውት የነበረውን መብትና በመሬቱ ላይ የሠፈሩት ሰዎች ላይ በጉልት ገዥነት ተሹመው የኖሩበት የመሬት ሥሪት ነው፡፡ ጉልተኛው በወረራ የሠፈረበትን ህብረተሰብ የመሬት ባለቤትነት የመሬት ይዞታና የመሬት አላባ የመጠቀም መብት በማሣጣት" ህብረተሰቡ ከመሬቱ ሠርቶ የሚያመርተውን እና አርብቶ የሚያሰባውን የሚወስድበት በአጠቃላይ ለጉልተኛው በጉልበቱ በማገልገል በአይነትና በገንዘብ ከአቅሙ በላይ አላባ እንዲከፍል የሚያስገድድበት የመሬት ሥሪት ነው፡፡ በጉልት የመሬት ሥሪት የመሬቱ ባለቤት አካባቢውን በጦርነትና በወረራ የያዘው ንጉስ ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን መሬቱን የማስተዳደር አላባውን የመሰብሰብና የመጠቀም መብቱ ደግሞ በዚያ አካባቢ የተሾመው ጉልተ ገዥ ነበር፡፡

ጉልተ ገዡው በበኩሉ ከመንግስት የተሰጠውን ወረታ ለመክፍል በአካባቢው ወታደራዊ እና አስተዳደራዊ ተግባራትን የማከናወን በየአካባቢው የሚነሱ ህዝባዊ አመፅ ለማስቆም በሚወሰዱ ወታደራዊ ጥቃቶች የመሣተፍና በጉልት ከተሰጠው መሬትና መሬቱ ከሰፈሩ ሰዎች በአይነት እና በገንዘብ የሚሰበሰበውን የመሬት አላባ ፍሬ በየደረጃው ላሉ ሹማምቶች የመጫንና የማካፈል ግዴታ ነበረበት፡፡ የጉልት የመሬት ሥሪት መሬታቸውና አካባቢያቸው በወረራና በጦርነት የተያዘባቸው ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ለጉልተ ገዡው ለብዝበዛ

ለጭቆናና ለባርነት የሚዳርግ የመሬት ሥሪት ነው፡፡ የጉልት መሬት ሥሪት የመሬቱ ባለቤት የነበሩትን ሰዎች ከመሬታቸው በንብረታቸውና በጉልበታቸው የማዘዝ እና የመጠቀም መብት ሙሉ በሙሉ በመግፈፍ ጉልተገኘ ሥር የሚኖሩ ብዙ ሰዎችን ለረሃብ ለጉስቁልና ለግርፋት ለድብደባና ለሞት የዳረገ አስከፊ የመሬት ሥሪትና የሥርዓቱ መገለጫ እንደነበረ በዚህ መስክ የተደረጉ ጥናቶች ያሣያሉ፡፡

## ሐ/ <u>የጉልተ ዕርሥት የመሬት ሥሪት</u>

የጉልተ ዕርስት የመሬት ሥሪት የፋሽስት ጣሊያን ጦር ከኢትዮጵያ ከወጣና አፄ ሀይለስላሴ ወደ አገር ከተመለሱ በኋላ የተዘረጋ የመሬት ሥሪት ነው፡፡ ንጉሱ ለአምስት ዓመት ያህል በነበረው የአርበኝነት ተጋድሎ ውስጥ ለአገራቸው አኩሪ ታሪክ ፈፅመዋል ለሚሏቸው “አርበኞች ወይም አርበኛ ናቸው” ተብሎ ለተመሠከረላቸው ሰዎች በጉልተገኘነት ይዘውት የነበረው መሬት በዕርስትነት እንዲይዙ በሽልማት መልክ ሰጡ፡፡ በዚህም ምክንያት ሽልማት ያገኙ ጉልተገኘዎች በጉልተገኘነት የያዙትን መሬት በሙሉ ዕርስትነት እና ባለቤትነት በመውሰድ የመሬቱ ባለቤት የነበረው ህዝብ መሬቱን ለቅቆ እንዲሰደድ ከፍተኛ የሆነ ግፍና ወንጀል ለመፈፀም ምክንያት የሆነ የመሬት ሥሪት እንደሆነ በበካርታ ጥናቶች ተረጋግጧል፡፡ በዚህ ሥርዓት ጉልተገኘዎቹ በፊት በጉልተኝነት ያልያዙትንና የማያስተዳድሩትን መሬት ሁሉ በዕርስትነት ለማስመዝገብ በኗሪዎቹ ላይ በርካታ የአስተዳደር በደል፣ የአካል ጉዳትና የሞት አደጋ ጭምር በማድረስ መሬቱን ያስለቀቁበትና አርሶ አደሮች በግፍ እንዲፈናቀሉ ያደረጉበት የመሬት ሥሪት ነበር፡፡

## መ/ <u>የገባር የመሬት ሥሪት</u>

የገባር የመሬት ሥሪት ማዕከላዊ መንግስት በሚያስተዳድራቸው በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች ተግባራዊ የሆነ የመሬት ሥሪት ነው፡፡ “የገባር የመሬት ሥሪት” ተግባራዊ መሆን የጀመረው ስለመሬት ግብር የወጣው አዋጅ ቁጥር 70/1937 ከወጣና የተሻሻለው የመሬት ግብር አዋጅ ቁጥር 117/1943 ወጥቶ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ነው፡፡ አዋጁ ተግባራዊ እንዲሆን ታስቦ የወጣው የሸዋ አማራ የርስት መሬት ላይ እንደሆነ የተመለከተ ቢሆንም አንድ ሰው መሬቱ የእሱ ዕርስት መሆኑ በሽማግሌ አስገምቶ አስመስክሮ ግብር የከፈለበት መሬት ላይ የባለቤትነት መብት የሚሰጥ በመሆኑ ይህንን የመሬት ሥሪት ተከትሎ በዕርስት ተካፋዮች መካከል ሰፊ የሆኑ ሙግት እንደተፈጠረና ባለሥልጣኖች

በሌሎች ሰዎች ወይም በሌላው የአገሪቱ ክፍል በጉልት በያዙት መሬት ላይ ግብር በመክፈል የመሬቱ ባለቤት መሆናቸውን ማስረጃ በማግኘት በመሬቱ ላይ የነበሩ አርሶ አደሮችን በማፈናቀል ወይም ጭሰኛ እንዲሆኑ በማድረግ ከፍተኛ የሆነ የፍትህ መጓደል ምክንያት የሆነ የመሬት ሥሪት እንደነበር በዚህ ርዕስ ዙሪያ ከተደረጉ ጥናቶች ለመረዳት ይቻላል፡፡

በዘውዳዊ ፈላጭ ቆራጭ ሥርዓት የመሬት ባለቤትነት በመንግስት በዕርስት፣ በጉልት፣ በጉልተዕርስትና በገባር የመሬት ሥሪት በሚተዳደርበት ወቅት አንደኛው ከሌላው የሚለይበት የተወሰኑ ነጥቦች ቢኖሩትም በአጠቃላይ ገፅታቸውና ይዘታቸው፣ በአፈፃፀማቸውና በውጤታቸው የሚመሳሰሉባቸው ሁኔታዎች እንደነበሩ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ይኸውም፣

- የመሬት ባለቤትነትና የመሬት ሥሪቱ በማናቸውም ጫፍ ይኖር የነበረውን አርሶ አደር የመሬቱ ባለቤትነትና የመሬት ይዞታና ተጠቃሚነት ዋስትና የሚያሳጣ፣
- አርሶ አደሩ የድካሙን ፍሬ ለባላባቶች እንዲያስረክብና በከፋ የጭሰኝነት የጉስቁልና እና የባርነት ኑሮ የዳረጉት የነበሩ መሆናቸው ነው፡፡

ይህንንም ግፍ የበዛበት አሠራር ለማስወገድ በተለያዩ ቦታ (ክፍለሀገር) የነበሩ አርሶ አደሮች ከባድ የአመፅ ንቅናቄ እና ትግል አድርገው የነበሩና የገበሬዎቹን ንቅናቄ ዋነኛ ምክንያት አጥንቶ ህጋዊ መፍትሄ ከመስጠት ይልቅ ንጉሱ ሠራዊታቸውን በማዝመት በርካታ አርሶ አደሮች እንዲገደሉ፣ ንብረታቸው እንዲቃጠልና እንዲዘረፍ ቤተሰባቸው እንዲበተን እንዳደረጉ የትግራይ ቀዳማዊ ወያኔ፣ የጎጃም ገበሬዎች አመፅና ሌሎች አካባቢዎች የተነሱ የአርሶ አደር አመፅ ንጉሱ ለማስቆም የወሰዱትን እርምጃ በመመርመር ለመረዳት ይቻላል፡፡

ለማጠቃለል በዘውዳዊ ፈላጭ ቆራጭ ሥርዓት የነበረው የመሬት ሥሪት ለአርሶ አደሩ የመሬት ባለቤነትም ሆነ የመሬት በይዞታነትና ተጠቃሚነት ምንም አይነት ዋስትና የማይሰጥ የአገሪቱ የእርሻ መሬት በጣት በሚቆጠሩ ሰዎች ባለቤትነትና አዛዥነት ሥር ያደረገና ሰፊውን አርሶ አደር ለጭሰኝነት እና ለባርነት የዳረገ እንደነበር ይኸም 1966 ዓ.ም የተቀሰቀሰው ህዝባዊ ቁጣና አብዮት መሠረታዊ ምክንያት የነበረ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

## 1.2. የመሬት ባለቤትነት የመሬት ይዞታና አጠቃቀም በደርግ ሥርዓት

ለብዙ ዓመታት ራሳቸውን "መኳንንትና ባላባት" ብለው በሚያሞካሹ የገዥው መደብ አባላት የመሬት ባለቤትነትና መሬቱን የመጠቀም መብቱ ተነፍጎ ለግፍ ለጭቆና ለረሀብ ለበሽታና ለእርዛት ተዳርጎ የኖረው ሰፊው አርሶ አደር የዘውዳዊን ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ከመንበሩ ላይ አሽቀንጥሮ ለመጣል ከሌሎች የአገሪቱ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ባደረገው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ አፄ ሀይለስላሴ ለሥልጣን ከወረዱ በኋላ ራሱን በአዋጅ ያቋቋመው የጊዛዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ከወሰዳቸው ሥር ነቀል እርምጃዎች አንደኛው የገጠርና የከተማ መሬትን የሕዝብ ሀብት ለማድረግ ያወጣቸው አዋጆችና አዋጆቹን ለማስፈፀም የወሰዳቸው ተግባራዊ እርምጃዎች ናቸው፡፡

ደርግ የገጠር መሬትን የሕዝብ ሀብት ለማድረግ አዋጅ ቁጥር 31/67 የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት የህዝብ ሀብት ለማድረግ አዋጅ ቁጥር 47/67 በማወጅ አዋጆቹን ለማስፈፀም ተግባራዊ የሆኑ እንቅስቃሴዎችን አድርጓል፡፡ የደርግ መንግስት በአዋጅ ቁጥር 31/67 ከየካቲት 25 ቀን 1967 ዓ.ም ጀምሮ የገጠር መሬት ሙሉ በሙሉ የህዝብ ሀብት መሆኑን፣ መሬት በማናቸውም የተፈጥሮ ሰው የንግድ ማህበር ወይም ሌላ ድርጅት በግል ባለሀብትነት ለመያዝ የማይችል መሆኑን ደንግጓል፡፡ ደርግ ባወጣቸው ህጎች በቀበሌ ኗሪ የሆነ ሰው፣

- ፆታ ሳይለይ ማናቸውም በእርሻ ሥራ ለመተዳደር ፈቃደኛ የሆነ ሰው ለራሱና ለቤተሰቡ ኑሮ በቂ የሆነ የገጠር መሬት የማግኘት መብት እንዳለውና የሚያገኘው መሬትም ከሩብ ጋሻ /አስር ሄክታር/ መሬት በላይ መብለጥ እንደሌለበት፣
- አዋጅ ከፀናበት ቀን ጀምሮ በባዕርስትና በጭሰኛ መካከል የነበረው ግንኙነት መፍረሱና ጭሰኛው ከማናቸውም ዕዳና ክፍያ ነፃ መሆኑን፣
- መሬትን በተመለከተ በመደበኛ ፍርድ ቤት ተይዘው የነበሩ ክሶች የተሠረዙና ፍርድ ቤቶች ማናቸውንም የገጠር መሬት ክርክር የመስማት ሥልጣን የሌላቸው መሆኑን፣
- አዋጁን ለማስፈፀም የገበሬዎች ማህበራት እንዲቋቋምና መሬት ለሁሉም አርሶ አደር በአዋጁ መሠረት ከተከፋፈለ በኋላ የሚነሱ የመሬት ክርክሮች በቀበሌ የፍርድ ሸንጎ በወረዳ ፍርድ ሸንጎና አውራጃ ፍርድ ሸንጎ ድረስ ከመጀመሪያ እስከ ይግባኝ ታይቶ የሚወሰን መሆኑን ደንግጓል፡፡

አዋጅ ቁጥር 31/67 ማንኛውም አርሶ አደር ሌላ ሰው በመቅጠር እርሻውን ለማሣረስ የማይችል መሆኑ በአንቀፅ /4/ በግልፅ የተደነገገ ሲሆን ሰው ቀጥሮ እርሻቸውን ለማሣረስ ስለሚችሉ ሰዎች ይደነግጋል፡፡

ደርግ አዋጁን ለማስፈፀም የመሬት ይዞታና አስተዳደር ሚኒስቴር ያቋቋመ ሲሆን የቀበሌ ገበሬ ማህበሮችን በማቋቋም የእርሻ መሬትን ለሁሉም አርሶ አደሮች በማከፋፈል ከገጠር የባላባትና የጭሰኛ ግንኙነት ሙሉ በሙሉ እንዲቋረጥ አድርጓል፡፡ ደርግ የንጉሣዊ ሥርዓት የነበረውን የተዛባ ግንኙነትና ፍትሐዊ ያልሆነ የመሬት ባለቤትነትና ሥሪት ሙሉ በሙሉ ለማስወገድ ማንም ሊክዳቸው የማይችላቸው ተጨባጭ እርምጃዎች የወሰደ ቢሆንም የቀበሌ ገበሬ ማህበር፣ የወረዳ እና የአውራጃ ገበሬ ማህበራት አዋጁን ለማስፈፀም ሲንቀሣቀሱ፣

- የእርሻ መሬትን ለአርሶ አደሮች በአዋጅ መንፈስ በኩል ደረጃ አለማካፈላቸው፣
- የቀበሌ የወረዳና የአውራጃ ገበሬ ማህበር ተመራጮች ለራሳቸውና ለወዳጆቻቸው ለቤተሰባቸውና ጉቦና ምልጃ ለሰጧቸው አርሶ አደሮች ለምና ሰፊ የሆነ የእርሻ መሬት መርጠው በመያዝና በመደልደል አድሎ መፈፀማቸውና ይህንን የሚቃወም አርሶ አደር "አድሀሪ" ፀረ አብዮተኛ ነው በሚል ከእርሻ መሬት እንዲነቀል እንዲታሰርና አንዳንድ ቦታም አላግባብ እንዲገደል በማድረግ አርሶ አደሩ የመሬት ድልድሉን በነፃነት እንዳይከታተልና እንዳይቆጣጠር የሰጡትን ብቻ ይዞ በፍርሀት እንዲኖር ማድረጋቸው፣
- አንዳንድ አካባቢዎች የመሬት ድልድል በየአመቱና በየሁለት ዓመቱ በማድረግ አርሶ አደሩ በጀመሪያው የመሬት ድልድል የተሰጠውን የእርሻ ማሣ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በመውሰድ ለሌላ አርሶ አደር በመስጠት እና በመቀያየር አርሶ አደሩ በድልድል ያገኘውን የእርሻ መሬት ላይ አስተማማኝ የይዞታና መሬቱን የመጠቀም መብት ኖሮት የመሬቱን ለምነት ለመጠበቅ በሙሉ ተነሳሽነት እንዳይሠራ ተገማች ያልሆነ ተደጋጋሚ የሆነ የመሬት ድልድልና ክፍያ ማድረጋቸው፣
- ተደጋጋሚ የመሬት ድልድል በመደረጉና ግልፅ የድንበር ወሰን ምልክት ባለመኖሩ መሬቱ የማን ይዞታ ነው? ለማን ነው የተሰጠው? በሚለው ጉዳይ ላይ አርሶ አደሩ የመሬቱ ባለይዞታ እኔ ነኝ እኔ ነኝ በሚለው ጉዳይ ከቀበሌ ፍርድ ሸንጎ ጀምሮ እስከ አውራጃ ፍርድ ሸንጎ በመከራከርና በመሟገት ጊዜውንና ጉልበትን እንዲያጠፋ መደረጉና አድሎና የፍትህ መጓደል የሚደርስበት መሆኑ፣

- በየአካባቢው ያለ አርሶአደሩ ፈቃድ ለተመሠረቱት የገበሬዎች አምራቾች የህብረት ሥራ ማህበር አርሶ አደሩ በመሬት ድልድል ወቅት የደረሰውን መሬት አሳልፎ እንዲሰጥና ያለውድ በግዴታ አባል እንዲሆን በማድረግና ከሚገኘው ምርትም በአይነት በአበል መልክ ብቻ ተከፋፍሎ እንዲወስድ የሚያስገድድ አሠራር ተግባራዊ መደረጉ፣
- አርሶ አደሩ በእርሻ መሬቱ ከሚያመርተው ምርት በገበያ ከሚያወጣው ዋና እጅግ ዝቅተኛ በሆነ ዋጋ ለእርሻ ሰብል ገበያ ድርጅት ምርቱን እንዲሰጥ የሚያስገድድ የኮታ አሠራር በመተግበር እና የእርሻ በሬ ወይም ከብት ከዋጋው በታች በሆነ ገንዘብ በኪሎ ተለክቶ ለመንግስት የሥጋ ፋብሪካዎች እንዲሸጥ ይገደድ የነበረ መሆኑ፣

አርሶ አደሩ የእርሻ መሬት በይዞታ ያገኘውን መሬቱን የማልማትና የመጠቀም መብት ዋስትና የማይሰጥ፣ በተቃራኒው አርሶ አደሩን የመሬቱን ለምነት ለመጠበቅ ቋሚ ከፍተኛ ገቢ የሚያወጡ ፍሪፍሬ እና ተክሎች የመትከል ፍላጎት ያጓደለ እና የመሬት ለምነት መራቆት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበራከተ ነበር፡፡

ከላይ ከተገለፁት በተጨማሪ፣

- የደርግ መንግስቱ ከህዝቡ እምነትና ፈቃድ ውጭ ከሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ያለ በቂ ዝግጅት ወደ ምዕራብ የአገሪቱ ክፍል ገበሬዎች እንዲሰፍሩ በማድረግ አርሶ አደሩን በግዴታ ከይዞታው በማፈናቀል የወሰደው እርምጃ፣
- በእናት አገር ጥሪ በወታደርነት ተፈልገው ለመዝመት ፈቃኛ ያልሆኑ አርሶ አደሮችና ብሄራዊ ውትድርና አልግሎት ተፈልገው ለጊዜው ከአካባቢው የተሰወሩ ገበሬዎችን የእርሻ መሬት በመንጠቅ ሀብታቸው እንዲወረስ በማድረግ፣
- ከአርሶ አደሩ ከፈቃዱና ከፍላጎቱ ውጭ ቤቱን በማፍረስ የመንደር ምሥረታ ፕሮግራም ተግባራዊ በማድረግና የመንደር ምሥረታ ፕሮግራሙን የሚቃወሙ አርሶ አደሮች የእርሻ መሬታቸው ተነጥቆ ለሌላ እንደሚሰጥ በማስፈራራት አልፎ አልፎ ይዞታቸውን በመንጠቅ

የቀበሌ ገበሬ ማህበር ሹማምንቶች እርምጃ የሚወስዱበት ሁኔታ ነበር፡፡

በደርግ ሥርዓት 1980 ዓ.ም የፀደቀው ህገ መንግስት ለአርሶ አደሩ የእርሻ መሬት የማግኘት እና መሬቱን የመጠቀም መብት ዋስትና አይሰጥም፡፡ የአርብቶ አደሩና አርሶ አደሩ ህይወት ከመሬት ይዞታ ጋር ትልቅ ቁርኝት ያለው ቢሆንም 1980 ዓ.ም ህገ መንግስት አርሶ አደሩና የአርብቶ አደሩ የመሬት ባለይዞታና በመሬቱ የመጠቀም መብት ያለው መሆኑን አይደነግግም፡፡ ህገመንግስቱ የአርሶ አደሩንና የአርብቶ አደሩን የመሬት ባለይዞታነትና በመሬቱ የመጠቀም መብት ዕውቅና እና ጥበቃ የማይሰጥ ከመሆኑ በተጨማሪ የኢኮኖሚ ሥርዓት በማለት በምዕራፍ ሁለት ከአንቀፅ 9 እስከ አንቀፅ 18 በዘረዘራቸው የኢኮኖሚ ፖሊስ አቅጣጫዎች የአርሶ አደሩና የአርብቶ አደሩ የመሬት ይዞታና መሬቱን የመጠቀም መብት ለማረጋገጥ መንግስት የፖሊስ ሀሳብ የነበረው መሆኑን የሚያመለክትም የለውም፡፡ በተቃራኒው ህገ መንግስቱ የህብረት ሥራ ማህበራት ማጠናከር መንደር ምሥረታና የሠፈራ ፕሮግራም መንግስት የገጠሩን ህብረተሰብ ኑሮ ለማሻሻል የሚከተለው የፖሊስ አቅጣጫ መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡

በአጠቃላይ ደርግ በአዋጅ ቁጥር 31/67 በማወጅና አዋጁን ለማስፈፀም የሚያስችል ተግባራዊ እንቅስቃሴ በማድረግ በገጠር የባላባትና የጭሰኛ ግንኙነትን በማስቀረት በኩል መሠረታዊና ሥር ነቀል እርምጃ የወሰደ ቢሆንም የእርሻ መሬት ድልድልና ሽግሽግ በተደጋጋሚ በማድረግ እና ከላይ በዝርዝር የገለፅናቸውን ተግባራት በመፈፀምና የቀበሌ ፍርድ ሸንጎ ውሣኔ በፍርድ ቤቶች ታይቶ እንዳይታረም በማድረግ በገጠር ብልሹ አስተዳደር በሥልጣን አላግባብ መገልገልና ሙስና እንዲገነባ በማድረግ የአርሶ አደሩ የመሬት በይዞታ የመሆንና በመሬቱ የመጠቀም መብት የህግም ሆነ በተግባር ዋስትና የሌለው እንዲሆን አድርጓል፡፡ በዚህ ምክንያት አርሶ አደሩ በባለይዞታነት ስሜት ሀላፊነት ተሰምቶት የመሬቱን ለምነት ለመጠበቅና ለመጨመር የሚያስችል ሥራዎች እንዳይሠራ የሚያደርግ ለመሬቱ ለምነት መቀነስ ለአካባቢው መራቆት ምክንያት የሆነ መሆኑ በዚህ ዙሪያ የተደረጉ የመስክ ጥናቶች ያሣያሉ፡፡

## *1.3. የመሬት ባይዞታነትና የመጠቀም መብት በሽግግር ወቅት*

የደርግ መንግስትና ወታደራዊ ሀይል ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም ከሥልጣን ከተወገደ በኂላ የተለያየ አመለካከትና አቋም ያላቸው ድርጅቶችና የተለያዩ ህብረተሰብ ተወካዮች የሽግግር ወቅት ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ ኮንፈረንስ በማካሄድ የሽግግር ወቅት ቻርተር አፅድቀዋል፡፡

የሽግግር ወቅት ቻርተር መሠረት በማድረግ የክልልና የወረዳ መስተዳድሮች በአዋጅ ቁጥር 7/1984 ተቋቁመዋል፡፡ የሽግግር ወቅት መንግስቱ አገሪቱ በሽግግር ወቅትና ከዚያ በኋላ የምትከተላቸውን የፖለቲካ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፖሊስ አቅጣጫ ለኢትዮጵያ ህዝብና ለዓለም አቀፍ ህብረተሰብ ግልፅ በማድረግ በርካታ ተግባራዊ እርምጃዎችን ወስዷል፡፡ የሽግግር ወቅት መንግስት፣

- የአገሪቱን ኢኮኖሚ ከመንግስት ማዕከላዊ አመራር /የእዝ/ ኢኮኖሚ ወደ ነፃ ገበያ የኢኮኖሚ ሥርዓት ለማሸጋገር አስፈላጊውን ሁሉ እንደሚያደርግ፣
- የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት የመንግስትና የህዝብ ሀብት ሆኖ እንደሚቀጥል፣
- መሬት የኑሮ መሠረታቸው የሆነው አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች ለእርሻ ሥራ የሚያከናውኑበት መሬት የማግኘት መብት እንዳላቸውና የመሬት ባለይዞታነትና የመጠቀም መብታቸው መንግስት ህጋዊ ዋስትና እንደሚሰጥ፣
- በግዴታ የመኖሪያ ቤታቸውን አፍርሰው በደርግ መንደር ምሥረታ የሚኖሩ ገበሬዎች ወደቀድሞ ቦታቸው የመመለስና ቤታቸውን ሰርተው መኖር እንደሚችሉ፣
- ከፍላጎታቸውና ከፈቃዳቸው ውጭ በደርግ ሠፈራ ፕሮግራም አካባቢያቸውን የለቀቁ ገበሬዎች ወደትውልድ ሥፍራቸው የመመለስና የነበራቸውን የእርሻ መሬት በማረስ መጠቀም እንደሚችሉ፣
- በግዳጅ የእርሻ መሬታቸውን ይዘው በገበሬዎች አምራቾች የህብረት ሥራ ማህበር የተደራጁ አርሶ አደሮች ከማህበሩ የመውጣትና የእርሻ መሬት የማግኘት መብት እንዳላቸው ግልፅ ከማድረጉ በተጨማሪ ከላይ የተዘረዘሩትን ተግባራዊ ለማድረግ ፈጣን ተግባራዊ እንቅስቃሴ አድርጓል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በኢህአዴግ ሠራዊት ቀደም ብሎ ከደርግ አስተዳደር በተለቀቁ ቦታዎች ፍትሐዊ የመሬት ሽግሽግና ክፍፍል የተደረገ ሲሆን በሽግግር ወቅት የተቋቋሙት የወረዳና የክልል መስተዳድሮች በአንዳንድ ክልሎች በደርግ ጊዜ ተንሠራፍቶ የነበረውን ፍትሐዊ ያልሆነ የእርሻ መሬት ክፍያ ፍትሐዊ ለማድረግ የሚያስችሉ የመሬት ድልድልና ሽግሽግ በማከናወን በደርግ ጊዜ የነበሩ የቀበሌ ገበሬ ማህበር አኢወማና አኢሠማ ተመራጮችና ቤተሰቦቻቸው ይዘውት የነበሩትን ሰፋፊ መሬት መሬት ለሌላቸው አርሶ አደሮች ተከፍሎ እንዲሰጥ በማድረግ የመሬት ይዞታ ፍትሐዊ እንዲሆን ለማድረግ የሚያሰችል እርምጃ ወስደዋል፡፡

በአጠቃላይ በሽግግር ወቅት መሬት በመንግስትና በህዝብ ሀብት ሆኖ የሚቀጥል መሆኑ አርሶ አደሮች በፍትሐዊ የመሬት ክፍፍል ባገኙት የእርሻ መሬት የባለይዞታነትና በመሬቱ የመጠቀም መብት ህጋዊ ዋስትና እና ጥበቃ የሚሰጥ ስለመሆኑ ግልፅ አቋም በመያዝ ተግባራዊ እንቅስቃስ ተደርጓል፡፡

# ***ምዕራፍ ሁለት***

# ***የመሬት ባለይዞታ የመሆንና የመጠቀም መብት በኢፌዲሪ ህገ መንግስት***

## 2.1. ***የመሬት ባለሀብትና የመሬት ባለይዞታ የመሆን መብት***

ለግል ባለቤትነት ሰፊ ዕውቅና እና ጥበቃ የሰጠው የኢፌዲሪ ህገ መንግስት የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የህዝብ ብቻ እንደሆነና መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት እንደሆነ በአንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 3 በግልፅ ይደነግጋል፡፡ ህገ መንግስቱ የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት በማናቸውም ሰው የግል ባለቤትነት የማይያዝ መሆኑን ከመደንገጉ በተጨማሪ ለኢትዮጵያ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች መሬትን የማግኘት መብት ዕውቅናና ጥበቃ ሰጥቷል፡፡ ከዚህ አንጻር፣

- የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘት መብት እንዳላቸውና ከመሬታቸውም ያለመነቀል መብት ያላቸው መሆኑ ዝርዝር አፈፃፀሙ በህግ እንደሚወሰን በግልፅ ደንግጓል፣
- የኢትዮጵያ አርብቶ አደሮች ለግጦሽም ሆነ ለእርሻ የሚጠቀሙበት መሬት በነፃ የማግኘት መብት እንዳላቸውና ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብት ያላቸው መሆኑ ዝርዝሩ በህግ እንደሚወሰን ደንግጓል፡፡
- መሬት የመንግስት እና የህዝብ ሀብት መሆኑ ሣይነካ የግል ባሀብቶች በመንግስት የሚወሰነውን ክፍያ እየከፈሉ መሬቱን የማልማትና የመጠቀም መብታቸው እንደሚከበርላቸውና ዝርዝሩ በህግ እንደሚደነገግ በግልፅ ተደንግጓል፡፡

- ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በጉልበት ወይም በገንዘቡ መሬት ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም በመሬቱ ላይ ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት ያለው መሆኑንና ይኸ መብት ንብረቱን የመሸጥ፣ የመለወጥና የማውረስ መብት እንደሚያጠቃልል ይደነግጋል፡፡
- በከተማም ይሁን በገጠር የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ በመሬቱ ላይ ያፈራውን ንብረት የማንሣት፣ ባለቤትነቱን የማዛወር ወይንም ተገቢው ካሣ ክፍያ የመጠየቅ መብት ያለው መሆኑ በግልፅ ተደንግጓል፡፡

በኢፌዲሪ ህገ መንግስት በአንቀፅ 40 ከንዑስ አንቀፅ 4 እስከ ንዑስ አንቀፅ 8 የተደነገጉት ድንጋጌዎች የአርሶ አደሩንና የአርብቶ አደሩን ለኑሮው ዋስትና የሆነውን መሬት በነፃ የማግኘት የመሬቱ ባለይዞታ የመሆንና ያለበቂ ምክንያት ያለመነቀል መብት እንዳላቸው ከመሬቱ የሚነቀሉበት በቂ ምክንያት ባለ ጊዜ መሬቱን በማልማት ላደረጉት ቋሚ መሻሻልና በመሬቱ ላይ ተክለውና ኮትኩተው ላፀደቋቸው ቋሚ አትክልቶችና ሰብል በቂ ካሣ የማግኘት መብት እንዳላቸው ህገ መንግስታዊ ጥበቃ ዋስትና የሚሰጡ ናቸው፡፡

መንግስት የሚያወጣቸው ህጎች እነዚህን ህገ መንግስታዊ ዋስትና የተሰጣቸውን መብቶች በተሟላ ሁኔታ ለማስፈፀም የሚረዱ እንጂ እነዚህን መብቶች የሚጥሱና ዋስትና የሚያሣጡ መሆን እንደሌለባቸው ዝርዝር ህጎቹ ከህገ መንግስቱ ጋር የሚቃረኑ ሆነው ከተገኙ ተፈፃሚነት የሌላቸው መሆኑን ከድንጋጌዎቹ አቀራረፅና ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ 1 ለመረዳት ይቻላል፡፡

የኢፌዲሪ ህገ መንግስት መንግስት መሬትና የተፈጥሮ ሀብትን በሕዝብ ስም በይዞታው ስር በማድረግ ለህዝቡ የጋራ ጥቅምና እድገት እንዲውሉ የማድረግ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ በኢኮኖሚክ ነክ አላማዎች በግልፅ የደነገገ ከመሆኑ በተጨማሪ ባለው ፌዴራላዊ ቅርፅ መንግስት አደረጃጀት የመሬት የተፈጥሮ ሀብት የታሪክ ቅርሶች አጠቃቀምና ጥበቃን በተመለከተ ህግ የማውጣት ሥልጣን የፌዴራል መንግስት እንደሆነና ክልሎች የፌዴራል መንግስት በሚያወጣው ህግ መሠረት መሬትና የተፈጥሮ ሀብትን የማስተዳደር ሥልጣን እንዳላቸው በአንቀፅ እና በአንቀፅ 51(2) በግልፅ ደንግጓል፡፡

ህገ መንግስቱ የፌዴራል መንግስቱ የአርሶ አደሮችና የአርብቶ አደሮች በነፃ መሬት የማግኘት፣ የመሬት ባለይዞታ የመሆንና ያለመነቀል መብት ወጥ በሆነ ሁኔታ ለማረጋገጥ የሚችል የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ህግ እንዲያወጣና ክልሎች የፌዴራል መንግስት ያወጣውን ህግ መሰረት በማድረግ ሌሎች የህግ ማዕቀፎችን በማውጣትና አስፈፃሚ አካላትን በማደራጀት በክልሉ ውስጥ ያለውን መሬት የማስተዳደር ስልጣን ያላቸው መሆኑ በግልፅና በማያሻማ ቋንቋ ይደነግጋል፡፡

## 2.2 <u>*የመሬት ባለይዞታ የመሆን መብት በፌዴራል ህጎች*</u>

የፌዴራል መንግስት በህገ መንግስቱ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የመጀመሪያውን የፌዴራል የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ በ1989 ዓ.ም አውጥቷል፡፡ የመጀመሪያው አዋጅ 89/1989 ሲሆን የገጠር ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ ከተነደፈ በኂላ ፖሊሲውን በአግባቡ ሊያስተገብር በሚችል መልኩ አዋጁን ማሻሻል በማስፈለጉ የገጠር መሬት አጠቃቀምን በተመለከተ የተሻሻለው የፌዴራል አዋጅ ቁጥር 456/97 ወጥቷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የፌዴራል መንግስት በሚያከናውናቸው የመሰረት ልማት ሥራዎች ምክንያት ከይዞታቸው ለሚፈናቀሉ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች ሌሎች ባላባቶች ካሳ አከፋፈል የሚደነግግ የህግ ማዕቀፍ አዋጅ ቁጥር 455/99 እና አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስችል ደንብ ቁጥር 135/1999 በማውጣት ሥራ ላይ አውሏል፡፡

***እነዚህ የህግ ማዕቀፎች***

- የአርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ በነፃ መሬት የማግኘት መብት በማረጋገጥና የአርሶ አደሩን ከይዞታው ያለመፈናቀል መብት ጥበቃ በመስጠት፣
- አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ ከይዞታቸው ማፈናቀል የሚያስፈልግበት በቂ ምክንያት ሲኖር መሬቱን ለማልማት ያወጡትን ወጪና በመሬቱ ላይ ላለሙት ቋሚ ንብረትና ሰብል በቂ ካሳ እንደዚሁም ከይዞታቸው የተፈናቀሉ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች በመፈናቀሉ ምክንያት ለሚደርስባቸው ጉዳት ካሳ የሚያገኙበትን ሁኔታ በዝርዝር በመደንገግ፣

የህገ መንግስቱን መሰረታዊ ድንጋጌዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የህግ መሰረት ጥለዋል፡፡

## ሀ/ አዋጅ ቁጥር 456/97

የፌዴራል የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ በማናቸውም የገጠር መሬት ላይ ተፈፃሚነት ያለው የህግ ማዕቀፍ ሲሆን አዋጁ ሁለት አይነት ባህሪ ያላቸው ድንጋጌዎችን የያዘ ነው፡፡ እነርሱም፣

- ❖ ሁሉም ክልሎች ሊያከብሯቸውና ሊተገብሯቸው የሚገቡ አስገዳጅ የህግ ድንጋጌዎች፣
- ❖ ክልሎች እንዳላቸው ነባራዊ ሁኔታ ውሳኔ ሊሰጡባቸው የሚገቡ ፈቃጅ የህግ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡

በአዋጅ ቁጥር 456/97 መሠረት ሁሉም ክልሎች የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ዝርዝር የህግ ማዕቀፎችና ሲያወጡና የህግ ማዕቀፎቹን ሲያስፈፅሙ የሚከተሉትን መሰረታዊ መብቶች የማክበር ግዴታ አለባቸው፡፡

- ❖ በግብርና ሥራ የሚተዳደሩ አርሶ አደር፣ ከፊል አርብቶ አደርና አርብቶ አደሮች የገጠር መሬት በነፃ የማግኘት መብት ማረጋገጥ፣ (አንቀጽ 5(1)(ሀ)
- ❖ ህፃናት አካለ መጠን እስኪያደርሱ በሞግዚታቸው አማካኝነት የገጠር መሬት የመጠቀም መብታቸውን ማረጋገጥ፣(አንቀጽ 5(1)(ለ)
- ❖ ሴቶች የገጠር መሬት በነፃ የማግኘትና የመጠቀም መብታቸውን ማረጋገጥ፣ (አንቀጽ 5(1)(ሐ)
- ❖ የአርሶ አደሮች፣ ከፊል አርብቶ አደሮችና አርብቶ አደሮች በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ያለምንም ጊዜ ገደብ ማረጋገጥ፣(አንቀጽ 7(1)
- ❖ ማንኛውም የአርሶ አደር[1] ቤተሰብ አባል ከቤተሰቡ በስጦታ ወይም በውርስ ወይም አግባብ ካለው አካል የገጠር መሬት በይዞታ የማግኘት መብቱን ማረጋገጥ፡፡ (አንቀጽ 5(2)

[1] ለአጠቃቀም ከዚህ በኋላ አርሶ አደር የሚለው ቃል በሚጠቀስበት ቦታ ሁሉ ከፊል አርብቶ አደር፣ አርብቶ አደርን የሚያካትት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

- አርሶ አደሮች በማይፈናቀሉበት መልኩ በይዞታ የያዙትን መሬት የማከራየት መብት ማረጋገጥ፣ የኪራይ ውሉ አግባብ ባለው አካል መጽደቅ ያለበት መሆኑን ማረጋገጥ፣ (አንቀጽ 8(1-3)
- ማንኛውም ባለይዞታ በገጠር መሬት የመጠቀም መብቱን ለቤተሰቡ አባላት የማውረስ መብት ያለው መሆኑ፣ (አንቀጽ 8(5)
- ማንኛውም አርሶ አደር መሬቱን በአግባቡ የመንከባከብ ግዴታ ያለበት መሆኑና በመሬቱ ላይ ጉዳት ከደረሰ በመሬት የመጠቀም መብቱን ሊያጣ የሚችል መሆኑን፣ (አንቀጽ 10(1)
- ማንኛውም የገጠር መሬት ባለይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ሊሰጠው የሚገባ መሆኑን፣ መሬቱ በባልና ሚስት በጋራ የተያዘ ከሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ በሁለቱ የጋራ ባለይዞታዎች ስም መዘጋጀት ያለበት መሆኑ (አንቀጽ 6(3)እና (4)
- ቅድሚያ ለአርሶ አደሮች በመስጠት ኢንቨስተሮችና ሌሎች ድርጅቶች የገጠር መሬትን በሊዝ ወይም በሌላ መልኩ በማግኘት የመጠቀም መብት ለማረጋገጥ የሚችል አሰራር መከተል፣ (አንቀጽ 5(4)
- የገጠር መሬት በግል፣ በወል፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ስለመያዙ የተሟላ መረጃ መዝግቦ መያዝና ኘላን መስጠት፣
- የገጠር መሬት ባለይዞታ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል መሬቱን በመንግስት እንዲለቅ ሲደረግ በመሬቱ ላይ ላደረገው ማሻሻያና ላፈራው ንብረት ተመጣጣኝ ካሳ የማግኘት መብቱን ማረጋገጥና ተለዋጭ መሬት እንዲያገኝ ማድረግ፣ (አንቀጽ 7(3)
- የገጠር መሬት በሊዝ የተከራየ ባለ ሀብት መሬቱን የመጠቀም መብቱን እንደዋስትና የማስያዝ መብቱን ማረጋገጥ፣ (አንቀጽ 8(4)
- የገጠር መሬት ሽግሽግ ለማድረግ መሠረት የሚሆኑ ደንቦች መከተል፣ (አንቀጽ 9)
- የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ ማውጣትና ማስፈፀም፣ (አንቀጽ 13)
- የመሬት ተጠቃሚዎች ግዴታቸውን እንዲወጡ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣
- ከመሬት ይዞታና መጠቀም መብት ጋር በተያያዘ የሚነሱ አለመግባባቶችና ክርክሮች ቅድሚያ በስምምነትና በመግባባት የሚፈቱበትን ስርአት መዘርጋት፣ (አንቀጽ 12)

ክልሎች የመሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም የህግ ማዕቀፎች ሲያወጡም ሆነ ህጎችን ሲያስፈፅሙ በጥብቅ ሊያከብሯቸው የሚገቡ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡

በአዋጅ ቁጥር 456/99 መሠረት ክልሎች የራሳቸውን ነባራዊ ሁኔታ በማገናዘብ በህግ ሊያወጡባቸውና በተለያየ መንገድ ሊያስፈፅሟቸው የሚገቡ ጉዳዮች በተመለከተ፡-

- መሬት በነፃ የማግኘት መብት ያለው ምን መስፈርቶችን ያሟላ እንደሆነ መወሰን፣
- በገጠር የሚገኝ መሬት በግል ይዞታ የሚያዝ፣ የወልና የጋራ መሆናቸውን መለየትና መከለል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የወልና የጋራ መሬት ይዞታዎችን ወደ ግል ይዞታ ማዛወር የሚቻልበትን ሥርዓት መዘርጋት፣
- የገጠር መሬት በሊዝ የያዙ ኢንቨስተሮች፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት የመሬት ባለይዞታነትና መሬትን የመጠቀም መብት ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ መወሰን፣
- አርሶ አደሮች በኪራይ ሊያስተላልፉ የሚችሉትን የይዞታ መጠንና ኪራዩ ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ መወሰን፣
- የኪራይ ውል የሚመዘግብበትን ሁኔታ መወሰንና ማመቻቸት፣
- የመስኖ መሬት ሽግሽግና የመሬት ሽግሽግ ማካሄድ ለማካሄድ የሚያስችሉ ደንቦች ማውጣት፣
- የገጠር መሬት አነስተኛ ወለል መጠን መወሰን፣
- የመሬት ይዞታ አስመልክቶ የሚነሳ ክርክር የሚፈታበትን ሁኔታና ስልጣን ያላቸውን አካላት በህግ መደንገግ፣
- የመሬት አጠቃቀምና አስተዳደር ህግን የሚያስፈፅሙ አካላት ማደራጀት ናቸው፡፡

## ለ/ <u>አዋጅ ቁጥር 455/1997</u>

በአዋጅ ቁጥር 455/97 እና ደንብ ቁጥር 135/1999 መሠረት ማናቸውም አርሶ አደር የፌዴራል መንግስት በሚያከናውነው የልማት ተግባር ምክንያት ከይዞታው ከተፈናቀለ፣

- መሬቱ ላይ ለሚገኘው ንብረትና መሬቱ ላይ ለሚደረገው ቋሚ መሻሻል ካሳ የማግኘት መብት አለው፡፡ (አዋጅ ቁ 455 አንቀጽ 7)
- ከመሬት ይዞታው በዘላቂነት በመፈናቀሉ ምክንያት ካሳ የማግኘት መብት አለው፡፡ የመፈናቀያ ካሳው መጠን ይዞታውን የሚለቀው በቋሚነት ከሆነ በአምስት ዓመት ያገኘው አማካኝ ገቢ በአስር ተባዝቶ ይከፈለዋል፡፡ (አዋጅ ቁጥር 455 አንቀጽ 8)

- ❖ ከመሬቱ የሚፈናቀለው ለተወሰነ ጊዜ ከሆነ በአምስት ዓመት የሚያገኘው አመታዊ ገቢ መሬቱ እስከሚመለስ ጊዜ ድረስ ይከፈለዋል፡፡ ሆኖም ይህ ካሳ በዘላቂነት ከይዞታው ሲፈናቀል ከሚከፈለው መጠን መብለጥ የለበትም፡፡
- ❖ የካሳው መጠን በንብረት ገማቹ ኮሚቴዎች በአግባቡ ተገምቶ ካሳ እንዲሰጠው የመጠየቅና በገማች ኮሚቴዎች ውሳኔ ካልተስማማ አቤቱታውን አግባብ ላለው የክልል ወይም የከተማ የመሬት ነክ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አቅርቦ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡ በኮሚቴው ውሳኔ ካልተስማማ በ30 ቀናት ውስጥ ይግባኝ እንደሁኔታው ደረጃውን ጠብቆ በክልል ከሆነ ለመደበኛ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት፣ በአዲስ አበባ ወይም ድሬዳዋ ከሆነ ለከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡
- ❖ ከመሬቱ የተፈናቀለ ማንኛውም ባለይዞታ መልሶ እንዲቋቋም አቅም በፈቀደ ከሚመለከታቸው አካላት እገዛና ድጋፍ የማግኘት መብት አለው፡፡

አዋጅ ቁጥር 455/1997 መሬቱ ላይ ላለ ንብረት ግምት የተቀበለ አርሶ አደር የመፈናቀያ ካሳ የመጠየቅ መብቱ የተጠበቀ መሆኑና ሁለቱ የተለያዩ የካሳ አከፋፈል ስርዓቶች እንጂ የሚተካኩ የካሳ አከፋፈል ሥርዓቶች አለመሆናቸውን ይደነግጋል፡፡ በደንብ ቁጥር 135/1999 በመሬት ላይ ያለ ሰብል ዛፍና ተክል የግምት አገማመት ሥርዓትና የመፈናቀያ ካሳ የአገማመት ሥርዓት በተለያየ መንገድ የሚከናወን መሆኑን ግልፅ በሚያደርግ መንገድ ተደንግጓል፡፡

በአጠቃላይ የፌዴራል መንግስት አርሶ አደሮች፣ ከፊል አርብቶ አደሮችና አርብቶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘት መብት፣ መሬትን የመጠቀም መብት ለማረጋገጥ የሚያስችል ህግ ያወጀ ሲሆን አርሶአደሮች ለህዝበ ጥቅም ሲባል ከመሬታቸው መልቀቅ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ በመሬቱ ላይ ላፈሩት ሀብት መሬቱን ለማልማት ላወጡት ወጪ ካሳ የሚያገኙበትን ሁኔታና ከመሬቱ በመፈናቀላቸው ምክንያት የመፈናቀል ካሳ ክፍያ የማግኘት መብት ያላቸው መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ክልሎች የሚያወጧቸው ክልላዊ አዋጆችና ደንቦችና መመሪያዎች ይህንን የፌዴራል የህግ ማዕቀፍ መሠረት ያደረገና ህጉን ለማስፈፀም የሚችል መሆን አለበት፡፡

## ከባለቤትነት መብት በመለስ አርሶ አደሮች ከፊል አርብቶ አደሮችና አርብቶ አደሮች የመሬት ባለይዞታነትና የመሬት የመጠቀም መብት በደርግና በኢፌዲሪ ያላቸውን በንፅፅር ስንመለከተው

| ተ.ቁ | በደርግ ሥርዓት | በኢፌዲሪ |
|---|---|---|
| 1. | በአዋጅ ቁጥር 31/67 የተደነገገ ቢሆንም በ1980 በወጣው የደርግ ህገመንግስት መሬት በነፃ የማግኘትና የባለይዞታነት መብት ህገ መንግስታዊ ዋስትና እና ጥበቃ አልተሰጠውም፡፡ | መሬት በነፃ የማግኘትና ከመሬቱ ያለመፈናቀል መብት ህገ መንግስታዊ ዕውቅናና ጥበቃ ተሰጥቶታል፡፡ |
| 2. | መሬት ለማግኘት የእርሻ መሬት ይዞ ለመቆየት የቀበሌ ቋሚ ኗሪና ሌላ ምንም አይነት መተዳደሪያ የሌለው መሆኑ ግድ ነበር፡፡ | እስከ ሁለት ዓመት ድረስ በአካባቢው ባይኖርም የመሬት ባለይዞታ የመሆን መብቱ ህጋዊ ጥበቃ ተሰጥቶታል፡፡ |
| 3. | ተደጋጋሚ የመሬት ሽግሽግና ድልድል እንዲፈፀም ለቀበሌ ለወረዳና ለአውራጃ ገበሬ ማህበር ሰፊ ስልጣን ይሰጥ ነበር፡፡ | የመሬት ሽግሽግ ማድረግ የሚቻለው፣<br>• ወራሽ የሌላቸው የሞቱና ለቅቀው የሄዱ ሰዎች ሲኖሩና ባለይዞታ ያልተመደበበት መሬት ሲኖር፣<br>• የመስኖ መሬትን በአግባቡና በፍትሀዊነት ለመጠቀም፣<br>• በአርሶአደሮች ፍላጎትና ውሳኔ የመሬት ሽግሽጉ አማራጭ የሌለው ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡<br>ከዚህ ውጭ በተደጋጋሚ የሚደረግ የመሬት ሽግሽግና ድልድል ህጋዊ ክልከላ ተደርጎበታል፡፡ |
| 4. | አርሶ አደሩ የመሬት ይዞታውን ወይም የመጠቀም መብቱን እንዲያከራይ ወይም በእርሻ ሥራው የሌላ ሰው ጉልበት በመቅጠር እንዲጠቀም የሚፈቅድ አልነበረም፡፡ | አርሶ አደሩ ሙሉ ለሙሉ ከይዞታው በማያፈናቅል ሁኔታ የእርሻ መሬቱን የማከራየት ማናቸውንም ሰው ቀጥሮ የማሰራት መብት አለው፡፡ |
| 5. | አርሶ አደሩ የእርሻ መሬት የማውረስ እና | አርሶ አደሩ መሬቱን በስጦታና በውርስ የማስተላለፍ |

| | | |
|---|---|---|
| | በስጦታ የማስተላለፍ መብት አያረጋግጥም፡፡ | ህጋዊ ዕውቅና ያገኘ መብት አለው፡፡ |
| 6. | አርሶ አደሩ ይዞታው ለመሬት ሽግሽግ ለሌላ ሲሰጥበት ወይም በሌላ ምክንያት እንዲለቅ ሲደረግ በመሬቱ ላይ ላደረገው ቋሚ ማሻሻያ እና ንብረት ካሣ የሚያገኝበት ህጋዊ ሁኔታ አልደነገገም፡፡ | አርሶ አደሩ በሽግሽግ ወቅት ወይም ከይዞታው ሲፈናቀል በመሬቱ ላይ ላደረገው ቋሚ መሻሻል ለንብረቱና ለመፈናቀሉ ምክንያት ለሚደርስበት ጉዳት ካሳ የማግኘት መብት አለው፡፡ |
| 7. | የአርሶ አደሩን በመሬት የመጠቀም እና ባለ ይዞታ የመሆን እና የምርት ተጠቃሚ የመሆን መብት የሚጎዱ በርካታ ተግባራዊ ችግሮች ነበሩ፡፡ | አርሶ አደሩ መንግስት የሚያወጣውን የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ መሠረት በማድረግ መሬቱን የማልማትና የፍሬው ሙሉ ተጠቃሚ የመሆን መብት አለው፡፡ |
| 8. | አርሶ አደሩ ወደ ፍርድ ቤት የመሄድ መብት የለውም፡፡ | አርሶ አደሩ ይግባኙንና ቅሬታውን ለፍርድ ቤት የማቅረብ መብት አለው፡፡ |

በአጠቃላይ ስንመለከተው አርሶ አደሩ ከፊል አርብቶ አደሩና አርብቶ አደሩ መሬቱን ከመሸጥና ከመለወጥ ውጭ ያሉ መብቶቹ በኢፌዲሪ ህገ መንግስትና ህገ መንግስቱን ተግባራዊ ለማድረግ በወጡ ህግ ማዕቀፎች የተረጋገጡለት መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## መሬት በነፃ የማግኘት ይዞታና መሬትን የመጠቀም መብት በክልል የህግ ማዕቀፎች

የፌዴራል መንግስት የሚያወጣውን የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ህግ መሠረት በማድረግ የክልል መንግስታት መሬትና የተፈጥሮ ሀብትን የማስተዳደር ስልጣን እንዳላቸው በፌዴራል ህገ መንግስት አንቀጽ 52 ንዑስ አንቀጽ 2(መ) ተደንግጓል፡፡ የፌዴራል መንግስት በህገ መንግስቱ በተሰጠው ስልጣን መሰረት አዋጅ ቁጥር 456/1997 የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ያወጀ ሲሆን በአዋጁ አንቀፅ 17 ንዑስ አንቀፅ 1 የፌዴራል መንግስት ያወጣውን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ የተለያዩ የህግ ማዕቀፎችን በክልል ምክር ቤት በኩል የሚወጣ ስለመሆኑ ይደነግጋል፡፡ በዚህ መሰረት የትግራይ ክልል፣ የአማራ ክልል፣ የኦሮሚያ ክልልና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል አዋጆችንና ደንቦችን በማውጣት ተግባራዊ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ናቸው፡፡

በአራቱ ክልል ምክር ቤቶች የወጡ አዋጆች ለማሰባሰብ የተሞከረ ሲሆን በክልሎቹ ፀድቀው እየተሰራባቸው ያሉ ደንቦችና መመሪያዎች በተሟላ ሁኔታ ለማግኘት ባለመቻሉ በዚህ ፅሑፍ ለመዳሰስ አልተቻለም፡፡ ስለሆነም ክልሎች በፌዴራል የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅን መሰረት በማድረግ የወጡትን ክልላዊ አዋጅ መሰረታዊ ይዘትና ገጽታ እና ክልሎቹ ባፀደቋቸው የህግ ማዕቀፎች መካከል የሚታየውን አንድነትና ልዩነት ከዚህ በታች በአጭሩ በሰንጠረዡ ለማየት እንሞክራለን፡፡

| ተራ ቁ | ጉዳዩ | አማራ (አዋጅ ቁ 133/98) | አሮሚያ (አዋጅ ቁጥር 130/1999 | ደቡብ (አዋጅ ቁ 110/99) | ትግራይ (136/2000 |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መሬት የማግኘት መብት | • በክልሉ ያለ ማንኛውም 18 አመት የሞላው እና በግብርና ስራ መተዳደር የሚፈልግ፣ የጾታ ልዩነት ሳይደረግ መሬት ማግኘት ይችላል፡፡ (5(2)<br>• ወላጆቻቸውን ያጡ እድሜያቸው 18 አመት ያልሞላቸው ህጻናት መሬት በነጻ ማግኘት ይችላሉ፡፡ (6(2) | • በግብርና ስራ ለመተዳደር የሚፈልግ 18 አመትና ከዚያ በላይ የሆነ አርሶ አደር (5)(1)<br>• ሴቶች ከወንዶች እኩል መሬት የማግኘት መብት አላቸው፡፡ (5(2)<br>• እድሜያቸው የገፋ፣ ወላጅ የሌላቸው ህጻናት፣ አቅመደካሞች የመሬት ይዞታቸውን በማከራየት መጠቀም እንደሚችሉ ይደነግጋል፡፡ 6(14) | • 18 አመት የሞላው እና በግብርና ስራ መተዳደር የሚፈልግ፣ (5)(1)<br>• በግብርና ስራ መሰማራት የሚፈልጉ ሴቶች፣ (5(2)<br>መሬት የማግኘት መብት አላቸው፡፡<br>• ባሎቻቸው በመንግስታዊ ስራ ወይም በሌላ ስራ የተሰማሩ ሴቶች (5/7)<br>መሬት ይዞታ የመጠቀም መብት አላቸው<br>• ይዞታ ያላቸው ባል ወይም ሚስት በሌላ አካባቢ መኖር ወይም በሞት መለየት የቤተሰብን በይዞታ የመጠቀም መብት አያሳጣም፡፡ (5(9)<br>• ባልና ሚስት ከጋብቻ በፊት ያላቸውን የመሬት ይዞታ በጋብቻ ምክንያት አያጡም፡፡ (5(5)<br>• ወላጆቻቸውን ያጡ እድሜ 18 አመት ያልሞላቸው ህጻናት ይዞታቸውን በሞግዚታቸው አማካይነት መጠቀም | • በግብርና ስራ ለመተዳደር የሚፈልግ አርሶ አደር መሬት በነጻ ያገኛል፡፡ (5(1(ሀ)፡፡ ይሁንና ዝቅተኛው እድሜ ስንት መሆን እንዳለበት አይገልጽም፡፡<br>• በግብርና ስራ መሰማራት የሚፈልጉ ሴቶች መሬት የማግኘት መብት አላቸው፡፡ (5(1(ሠ)<br>• 18 አመት ያልሞላቸው በመሬት የመጠቀም መብት እንዳላቸው ያስቀምጣል፡፡ 5(1)(መ) |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ይችላሉ (5(8) | |
| 2 | የጎጆ መውጫ | • | | • | • 18 አመት የሞላቸውና ጎጆ መውጫ ያላገኙ፣ በስደት የቆዩና ወደቀበሌያቸው ለሚመለሱ ለጎጆ መውጫ ተብሎ ከተከለለው መሬት ይሰጣቸዋል፡፡<br>• ለጎጆ መውጫ የሚሰጥ ቦታ 20x20 ሜትር ይሆናል፡፡<br>• ቅድሚያ በስደት ቆይተው ለሚመለሱ ይሰጣል፡፡<br>• ቀጥሎም እድሜያቸው ከፍ ላለ ይሰጣል፡፡<br>• ቀጥሎም በአንድ ቀን ከተወለዱት በእጣ ይሰጣል፡፡<br>• የተከለለ የጎጆ መውጫ በሌለበት አካባቢ ወላጆች የጎጆ መውጫ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ (25)<br>• ማንኛውም አርሶ አደር ለጎጆ መውጫ ከተፈቀደለት ውጪ በሚታረስ መሬት ላይ የመኖሪያ ቤት መስራት የተከለከለ ነው፡፡ እንዲፈርስ ይደረጋል፡፡ (11(1(ሠ) |
| 3 | መሬት ይዞታን በስጦታ ማስተላለፍ | • አነስተኛ መጠን ያለው መሬት እያረሰ ያለ ልጅ የልጅ ልጅ ወይም የቤተሰብ አባል ከሆነ<br>• ተቀባዩ የባለስልጦታውን መሬት እያረሰ ወይም ሌላ ስራ እየሰራ ስጦታው ከመሰጠቱ በፊት ለ3 | ማንኛውም አርሶ አደር<br>• ለቤተሰብ አባሉ ወይም<br>• መሬት ለሌላቸው ወይም ሌላ ገቢ ለሌላቸው ልጆቹ፣<br>በመሬት የመጠቀም መብቱን በስጦታ ሊሰጥ ይችላል፡፡ (9(5)<br>• የቤተሰብ አባል ማለት የመሬት | • ማንኛውም የአንድ አርሶ አደር ቤተሰብ አባል ከቤተሰቡ በስጦታ መሬት ማግኘት ይችላል፡፡ (5(11)<br>• የቤተሰብ አባል ማለት የይዞታ ባለመብቱን መተዳደሪያ በመጋራት በቋሚነት አብሮ የሚኖር ነው፡፡ | • ማንኛውም በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ያለው አርሶአደር ከቤተሰቡ በስጦታ መሬት ማግኘት ይችላል፡፡ (5(2)<br>• መሬትን በስጦታ ማስተላለፍ የሚቻለው የገጠር መሬት ለሌለው ልጅ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ተከታታይ አመታት ሰጪውን በነጻ ሲጦር የቆየ በስጦታ ሊያገኝ ይችላል፡፡ (17(1)<br>• የቤተሰብ አባል ማለት ከመሬት ባለይዞታው ጋር በቋሚነት አብሮ የሚኖርና የራሱ የሆነ ቋሚ መተዳደሪያ የሌለው የይዞታ ባለመብቱን አርሶ አደር ገቢ በመጋራት የሚተዳደር ማንኛውም ሰው ነው፡፡ (2(6)<br>• ማንኛውም ሰው የይዞታ መብቱን በቋሚነት የተጠቃሚነት መብቱን ለተወሰነ ጊዜ ለሌሎች ሰዎች ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡ (17(2)<br>• ድርጅቶች በመሬት የመጠቀም መብታቸውን ለተወሰነ ጊዜ በስጦታ ማስተላለፍ ይችላሉ፡፡ (17(4)<br>• ስጦታ በጽሁፍ መደረግ አለበት፡፡ በባለስልጣኑ መስሪያ ቤት መመዝገብ አለበት፡፡ (17(5-6) | ባለይዞታው ልጆች እና ከመሬት ባለይዞታው ጋር አብረው የሚኖሩ ሌላ ገቢ የሌላቸው ጥገኞች ማለት ነው፡፡ (2(16) | (2(7) | ወይም ወላጅ ብቻ ነው፡፡ (5(3)(ሀ)<br>• በወረዳ ወይም በንኡስ ወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት ይመዘገባል፣ ቅጂ በቀበሌ መሬት አስተዳደር ኮሚቴና በወረዳ ዴስክ ይቀመጣል፡፡ |
| 4 | መሬት ይዞታን በውርስ ማስተላለፍ | • በግብርና ስራ መተዳደር ለሚፈልግ ማንኛውም አርሶ አደር በኑዛዜ ማስተላለፍ ይቻላል፡፡ (16(1)<br>• ለውርስ አላማ ሲባል የገጠር ኑሮአቸውን ለመደጎም ዝቅተኛ ገቢ የሚያስገኝ ስራ እየሰሩ በከተማ የሚቀመጡም ሰዎች እንደአርሶ አደር | የገጠር መሬት ባለይዞታ፣<br>• በመሬት የመጠቀም መብቱን በውርስ ህግ መሰረት መብት ላላቸው የቤተሰብ አባላት ሊያስተላልፍ ይችላል (9(1)<br>• ይሁንና ሌላ መተዳደሪያ ለሌላቸው ወራሾች ቅድሚያ ይሰጣል፡፡ (9(2)<br>• ወራሽ የሌለውን መሬት መንግስት | • ማንኛውም የአንድ አርሶ አደር ቤተሰብ አባል ከቤተሰቡ በውርስ መሬት ማግኘት ይችላል፡፡ (5(11) እና 8(5)<br>• በውርስ ምክንያት መሬቱ ለወራሾች ሲከፋፈል ለእያንዳንዱ የሚደርሰው ከዝቅተኛው ማሳ መጠን በታች ከሆነ፣ ይህ እንዳይሆን | ባለይዞታ ሲሞት፣<br>• መሬት የሌለው ልጁ በቅድሚያ ወራሽ ይሆናል<br>• ሚች ልጅ የሌለው ከሆነ መሬት የሌለው ወላጁ ይወርሰዋል፡፡<br>• ጉዲፈቻ ልጅ ከጉዲፈቻ አድራጊው ልጆች እኩል የመውረስ መብት አለው፡፡<br>• የሚካሄደው ወርስ ከሁለተኛ ደረጃ ማለፍ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ይቆጠራሉ፡፡ (16(2)<br>• በኑዛዜ የማውረስ መብት አካለመጠን ያላደረሰውን ልጁን ወይም ቤተሰብ ከወራሽነት መብት ከህግ ውጪ የሚነቅል ወይም የተናዛዡን የትዳር ጋደኛ የሚጎዳ ከሆነ በህግ ፊት አይጸናም፡፡ (16(3)<br>• ሳይናዘዝ ከሞተ በግብርና ለሚተዳደር ወይም ለመተዳደር ለሚፈልግ ልጁ ወይም ቤተሰብ ይተላለፋል፡፡ (16(5)<br>• ልጅ ወይም ቤተሰብ የሌለው በክልሉ ለሚኖሩ ቤተሰቦቹ (ያላቸው ይዞታ ከፍተኛው ጣሪያ ያልደረሰ ከሆነ) ሊወርሱ ይችላሉ፤፤(16(6)<br>• በውርስ ምክንያት መሬቱ ሲከፋፈል በደንቡ ከተወሰነው የአንድ ማሳ አነስተኛ መጠን በታች ከሆነ መሬቱን በጋራ መጠቀም እንጂ መከፋፈል አይችሉም፡፡ (16 (8)<br>• ወራሽ ያልተገኘለት ቦታ ለአዲስ አመልካቾች ይከፋፈላል፡፡ (16(9) | ወስዶ መሬት ለሌላቸው ወይም ለሚያንሳቸው ያከፋፍላል፡፡ (9(3)<br>• ወራሾች ሲከፋፈሉ ከዝቅተኛው ማሳ በታች የሚሆን ከሆነ ወራሾች በጋራ ወይም በሌላ መንገድ እንዴት ሳይከፋፈል መጠቀም እንደሚችሉ ይወስናሉ፡፡ (9(3) | በክልሉ በሚወጣ ዝርዝር ደንብ እንደሚወሰን ይደነግጋል፡፡ (11(3) | የለበትም፡፡ (ይሁንና በዚህ አዋጅ መሰረት የሚወርስ ልጅ የሌለው ከሆነ የሟች የልጅ ልጆች ይወርሳሉ)<br>• የራሱ የመሬት ይዞታ ያለው ወይም ከግብርና ውጪ ኑሮውን የለወጠ ሰው ከጎጆ መውጫ በስተቀር መሬቱን መውረስ አይችልም፡፡<br>• በከተማ የሚኖሩ ልጆች የገጠር መሬት መውረስ አይችሉም፡፡<br>• ወራሽ የሌለ ከሆነ በቀበሌ ገጠር መሬት አስተዳደር ኮሚቴ መሬት ለሌላቸው እንዲታደል ያደርጋል፡፡ ይሁንና ቅድሚያ መሬት ለሌለውና በሟቹ ቤት ያደገ ወይም ጧሪ ለሆነ ሰው ቅድሚያ ተሰጥቶት ሊሸጋሽግ ይገባል፡፡<br>(አንቀጽ 17)<br>• አርሶ አደሮች መሬትን ሊለዋወጡ ይችላሉ፡፡<br>• በውርስ ምክንያት መሬቱ ከተቀመጠው ዝቅተኛ በታች የሚከፋፈል ከሆነ በጋራ እንዲጠቀሙበት ይመቻቻል፡፡ ካልተስማሙ እጣ ተጥሎ ለደረሰው ይወስዳል፡፡ (17(3) |
| 5 | በገጠር መሬት ላይ የተፈሩ ቋሚ ሀብቶች ላይ ያለመብት | • የይዞታ መብት በመሬቱ ላይ ንብረት ማፍራት፣ ያፈራውን ንብረት የማስተላለፍ መብት እንደሚያካትት ተደንግጓል፡፡ (2(8) | • በመሬቱ ላይ ያሉ ቋሚ ተክሎች እንደቡና የቡና፣ ማንጎ፣ አቮካዶ፣ ፓፓያ ብርቱካን የመሰሉ ቋሚ ተክሎችን መሸጥ አይችልም፡፡ (6(2)<br>• ከእነዚህ ተክሎች የሚገኙ | • በመሬቱ ላይ በገንዘቡና በጉልበቱ ያፈራውን ሀብት የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማስያዝ፣ የመስጠት፣ የማውረስ፣ በዋስትና የማስያዝ መብት አለው፡፡ (8(6) | • በሚታረስ መሬት ላይ የሚገኙ እንደ እጣን፣ ዐየ፣ዋንዛ፣ ቆንጥር፣ ወይራ፣ጥድ፣ የሙጫ ዛፍ ወዘተ መቀረጥ የተከለከለ ነው፡፡ (13(3)<br>• የእጣንና የሙጫ ዛፎች |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ምርቶችን ከሶስት አመት ላልበለጠ ጊዜ እንዲሁም ከመሬቱ ግማሽ ይዞታ ካልበለጠ መሸጥ ይቻላል፡፡ (6)(3)<br>• በገጠር መሬት ላይ ያለ ህንጻ ወይም ቤት የገዛ፣ ህንጻውን ወይም ቤቱን ከገጠር መሬቱ ላይ የማንሳት ግዴታ አለበት፡፡ (6(8) | | ምርትን በመሸጥ ወይም በማከራየት መጠቀም ይቻላል፡፡ (13(4)<br>• በፍላጎቱ በመሬቱ የመጠቀም መብቱ ያቋረጠ በመሬቱ ላይ ያፈራውን ሀብት የመውሰድ መብት አለው፡፡ ሆኖም ለቋሚ ተክሎች ካሉት ግምቱን እንዲከፈለው ይደረጋል፡፡ (14(7) |
| 6 | የእርሻ መሬትን ማከራየት | • ከሶስት አመት ለሚበልጥ ጊዜ የሚደረግ የኪራይ ውል በጽሁፍ መደረግ አለበት፡፡ መመዝገብ አለበት፡፡(18(1 እና 5)<br>• ከፍተኛው የኪራይ ዘመን 25 አመት ነው፡፡ ጊዜው ሲያልቅ እንደገና ሊታደስ ይችላል፡፡ (18(6-7)<br>• በግልጽ በስምምነቱ ካልተገለጸ በስተቀርተከራዩ ለሌላ ሰው መልሶ ሊያከራይ አይችልም፡፡ (18(9)<br>• | አርሶ አደሩ ከግማሽ የማይበልጠውን ይዞታውን ሊያከራይ ይችላል፡፡ (10(1)<br>• በልማዳዊ እርሻ ለሚታረስ ከሶስት አመት ላልበለጠ፣<br>• በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ለሚታረስ ከ15 አመት ላልበለጠ ሊያከራይ ይችላል፡፡ (10(2)<br>• የኪራይ ውሉ ዋጋ የሚኖረው ከተመዘገበና በኦሮሚያ እርሻ ገጠር ልማት ቢሮ ከጸደቀ ብቻ ነው፡፡ (10(3)<br>• በሚደረገው ውል ላይ በመሬቱ ላይ ባለመብት የሆኑ ሁሉ ሊስማሙ ግዴታ ነው፡፡ (10(6)<br>• | • ለአርሰ አደር እስከ 5 አመት ሊያከራይ ይችላል፡፡ (8(1(ሀ)<br>• አመታዊ ሰብሎችን ለሚያመርቱ ባለሀብቶች እስከ 10 አመት ማከራየት ይችላል፡፡ (8(1(ለ)<br>• ቋሚ ተክልን ለሚያመርቱ እስከ 25 አመት ማከራየት ይችላል፡፡ (8(1(ሐ)<br>• የኪራይ ውሉ በመሬቱ የመጠቀም መብት ያላቸው የቤተሰብ አባላት የጋራ ይሁንታ ማግኘትና መመዝገብ አለበት፡፡ (8(2)<br>• ከባለሀብት ጋር በመሬቱ ይዞታ ሽርክና ከባለሀብት ጋር መግባት ይችላል፡፡ (8(3)<br>• | የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የተሰጠው አርሶ አደሩ ከግማሽ የማይበልጠውን ይዞታውን ሊያከራይ ይችላል፡፡ (6(1)<br>• ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ለሚጠቀም ተከራይ እስከ 20 አመት<br>• ልማዳዊ የእርሻ ዘዴ ለሚጠቀም ተከራይ እስከ ሶስት አመት ይሆናል፡፡ (6(3)<br>• ውለታው በወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት ይመዘገባል፡፡ (10) |
| 7 | የእርሻ መሬትን መለዋወጥ | • | • | • ይዞታቸውን አርሶ አደሮች ሊለዋወጡ ይችላሉ፡፡ (11(4) | • መሬት መለዋወጥ የሚፈልጉ አርሶ አደሮች በስምምነት ሊለዋወጡ ይችላሉ፡፡ (19(1)<br>• ወራሽ የሌለው የሟች ይዞታ ልጁ ቅድሚያ ተሰጥቶት ሊለውጥ ይችላል፡፡ (19(5) |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 8 | መሬት ሽግሽግ | • 80 በመቶ የሚሆኑና በአንድ ቀበሌ ውስጥ የሚገኙ ባለይዞታዎች የመሬት ክፍፍል እንዲካሄድ ጠይቀው ከሆነ ጥያቄው በቀረበበት የይዞታ ሽፋን የመሬት ሽግሽግ ሊካሄድ ይችላል፡፡ ተፈጻሚነቱም ውሳኔውን ባሳለፉት ባለይዞታዎች ላይ ብቻ ይሆናል፡፡ (8(2)<br>• በመስኖ የሚለማ መሬት ላይ ግን የመሬት ሽግሽግ ወይም ክፍፍል ሊደረግ ይችላል፡፡ (8(3)<br>• ለሴቶች፣ አቅመደካሞች፣ ለወላጅ አልባ ህጻናት ይሰጣል፤፤(5(6)<br>• | በመስኖ የሚለማ መሬት ካልሆነ በስተቀር የመሬት ሽግሽግ አይኖርም፡፡ (14(4) ያልተያዙ መሬቶች መሬት ለሌላቸው ወይም መሬት ላነሳቸው ሊደላደል ይችላል፡፡ (14(2) | • ወራሽ የሌላቸው፣ ወይም መሬቱን ጥለው ከሄዱ ሰዎች ተወስዶ መሬት ለሌላቸውና ላነሳቸው ባለይዞታዎች ይደለደላል፡፡ (9(1)<br>• ከመስኖ ልማት ጋር በተያያዘም ድልድል ይኖራል፡፡ (9(2) | • በሰፈራ ወይም በሌላ ምክንያት የተለቀቁ መሬቶች ለሌሎች ይደለደላሉ፡፡ (22(1)<br>•ተራሮችና ቦረቦሮች የመሬት መሸርሸርን በማያስከትል መንገድ በሽግሽግ ስራ ላይ ሊውሉ ይችላሉ፡፡ (22(2)<br>•በመስኖ በሚለማ መሬት ሽግሽግ ሊደረግ ይችላል፡፡ (23) |
| 9 | የገጠር መሬት ይዞታና የመጠቀም መብት ቀሪ የሚሆንባቸውን ሁኔታዎች፣ (በፈቃድና ያለፈቃድ) | የመሬት ባለይዞታው፣<br>•ከግብርና ውጪ የተሰማራና ቋሚ መተዳደሪያ ያለው ከሆነ (12(1(ሀ)<br>•በተከታታይ ከ5 አመት በላይ ወይ ሳያከራይ ከመኖሪያው ቦታ የጠፋና የት እንዳለ ያልታወቀ ከሆነ፣ (12(1(ለ)<br>•በተከታታይ ከ3 አመታት በላይ መሬቱን በጥቅም ላይ ያላዋለ ከሆነ፣ወይም በመስኖ የሚለማ መሬት ከአንድ አመት በላይ በጥቅም ላይ ያልዋለ ከሆነ (12(1(ሐ)<br>•መሬቱን በእንክብካቤ ባለመያዙ በመሬቱ ላይ ጉዳት የደረሰ | • ያለበቂ ምክንያት መሬታቸው የሚገኝበትን ቦታ ከሁለት አመት በላይ ለቀው ከሄዱ፣<br>•በራሱ ፈቃድ መሬቱን ለቀቆ ከሆነ፣<br>•መሬቱን ባለመንከባከብ ጉዳት አድርሶ ከሆነ፣ መሬቱ ሊወሰድበት ይችላል፡፡ (6(16))<br>• ለህዝብ ጥቅም ሲባል መሬቱን መውሰድ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ (6(11)<br>ዝርዝር ደንብ እንደሚወጣም ያመለክታል፡፡ | • መሬትን በአግባቡ የመጠበቅና የመንከባከብ ግዴታ አለበት፡፡ በመሬቱ ላይ ጉዳት ካደረሰ ና በቅጣት ብቻ ሊታለፍ የማይችል ሲሆን የመጠቀም መብቱን ሊያጣ ይችላል፡፡ (13(12)<br>• መሬትን ያለበቂ ምክንያት አግባብ ባለው አካል ከሚሰጠው የጊዜ ገደብ በላይ ጦም በማሳደር በመሬት የመጠቀም መብቱን ያጣል፡፡ (13(13)<br>• ለህዝብ ጥቅም አስፈላገ ሲሆን፣ (13(11) | • ያለበቂ ምክንያት መሬታቸው የሚገኝበትን ቦታ ከሁለት አመት በላይ ለቀው ከሄዱ መሬቱ ተወስዶ ለሌላ ይደለደላል፡፡(12(1)<br>• ይሁንና የሚከተሉትን አይጨምርም 1) የመከላከያነ የፖሊስ አባላት፣ 2) የተሰው ታጋዮች መሬት ወራሾች ወይም ተጠቃሚዎች፣ 3) በጋብቻ ምክንያት ወደሌላ አካባቢ የሄዱ፣ 4) በትምህርት ምክንያት የለቀቀ፣ 5) የህዝብ ተወካዮች ሆነው የለቀቁ፣ ወዘተ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | እንደሆነ የቃልና የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡ (21(1)<br>•በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሰረት ካላሻሻለ መሬትን ለተወሰነ ጊዜ ለመንከባከብ ግዴታ ለሚገባ ሰው በኪራይ እንዲሰጠውይወሰናል (21(2)<br>•ጥፋቱ በተመሳሳይ ሁኔታ ከተደገመ መሩቱን እንዲለቅ ሊደረግ ይችላል፡፡ (21(3)<br>•ይዞታውን በራሱ ፈቃድ የተወ መሆኑን ያሳወቀ እንደሆነ፣ (12(1(መ)<br>•ለህዝብ ጥቅም ሲባል ይዞታውን እንዲለቅ የሚደረግ ከሆነ፣(28(1) | | | • የወር ገቢያቸው ከብር አንድ ሺህ በታች የሆኑ በመሬት ይዞታቸው የመጠቀም መብት ይኖራቸዋል፡፡ ይሁንና በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ እንዲመርጡ ይደረጋል( 12(3)<br>• መሬቱን በአግባቡ ያልተንከባከበና በመሬቱ ላይ ጉዳት አድርሶ በተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ሊያስተካከል ካልቻለ የመጠቀም መብቱ ሊቋረጥ ይችላል፡፡ (አንቀጽ 14)<br>• ማንኛውም በመስኖ የሚጠቀም መሬት ለሁለት ተከታታይ አመታት በመስኖ ተጠቅሞ ካላለለማ መሬቱ ተወስዶ ለሌላ ሊሸጋሸግ ይችላል፡፡ 23(10)<br>• ለህዝብ ጥቅም ሲባል መሬቱን እንዲለቅ ሊደረግ ይችላል፡፡ (21(1) |
| 10 | መሬት በፍርድ ቤት ውሳኔ የማይያዝና የማይከበር መሆኑ፣ | | በፍርድ ቤት ውሳኔን ለማስፈጸም ማንኛውም የገጠር መሬት ባለይዞታ ከይዞታው አይፈናቀልም፣ ወይም ወይም ለእዳ መክፈያ በሚል ይዞታው ለሌላ አካል ሊተላለፍ አይችልም፡፡ (6(5) | | |
| 11 | የይዞታ ማረጋገጫ | •የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ይሰጠዋል፡፡ የባለይዞታው በህግ የተጠበቀ መብት ማረጋገጫ ነው፡፡(24(1)<br>• መሬቱ የባልና የሚስት የጋራ ከሆነ ደብተሩ በሁለቱ ስም | • የገጠር መሬት ባለይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ይሰጠዋል፡፡ (15(4)<br>• መሬቱ የተያዘው በባልና ሚስት በጋራ ከሆነ በሁለቱ ስም ደብተሩ ይዘጋጃል፡፡ (15(8) | • መሬቱ የተያዘው በባልና ሚስት በጋራ ከሆነ ደብተሩ በሁለቱ ስም ይዘጋጃል፡፡ (6(4)<br>• ባሎቻቸው በመንግስታዊ ስራ ወይም በሌላ ስራ ተሰማርተው | •የመሬት ባለይዞታው የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ይሰጠዋል፡፡ ባልና ሚስት የጋራ ባለይዞታ ከሆኑ ደብተሩ በሁለቱ ስም ተዘጋጅቶ ይሰጣቸዋል፡፡ (5(1(ሐ) |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ይዘጋጃል፡፡ (24(2)<br>• ተቃራኒ ማስረጃ እስካልቀረበ ድረስ የይዞታ ማረጋገጫ በስሙ የተሰጠው ሰው የመሬቱ ህጋዊ ባለይዞታ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡ (24(4) | • | የሚገኙ ሴቶች የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ይሰጣቸዋል፡፡ (6(5)<br>• ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት ያለይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የገጠር መሬትን መጠቀም አይችልም፡፡ (13(14) | • |
| 12 | የግል ባለሀብቶች መሬት የማግኘት መብት | ከመንግስት በኪራይ ወይም ከመሬት ባለይዞታ በስምምነት ማግኘት ይችላሉ፤፤(6(3) | መነግስት በአርሶ አደሮች ያልተያዘ መሬትን ለግል ባለሀብቶች መሬት በኪራይ ሊሰጥ ይችላል፡፡ (11) | መንግስት ለአርሶ አደሮች ቅድሚያ በመስጠት መሬት ለግል ባለሀብቶች በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ይኖራቸዋል፡፡ (5(15) | • መንግስት እስከ 50 አመት በሚቆይ የኪራይ ውል ለባሀብቶች መሬት ሊያከራይ ይችላል፡፡ (7)<br>• ባለሀብቱ የተከራየውን ለሌላ ማከራየት የተከለከለ ነው፡፡ (9(3)<br>• የእርሻ ኢንቨስትመንት መብትን ምርት መስጠት ከመጀመሩ በፊት ማስተላለፍ አይቻልም( 15) |
| 13 | በእዳ ዋስትና አድርጎ ስለማስያዝ | • በሊዝ መሬት ያለው የመጠቀም መብት በእዳ ዋስትና ሊያዝ ይችላል፡፡ (19(1)<br>• በዋስትና የተያዘን የሊዝ መሬት አበዳሪው ካልተስማማ ማከራየት፣ በሌላ መሬት መለወጥ ወዘተ ማድረግ አይቻልም፡፡ (19(3)<br>• በእዳ ዋስትና ለማስያዝ የሚደረግ ስምምነት በጽሁፍ መሆን አለበት፣ መመዝገብ አለበት፡፡ (19(4)<br>• በመሬት የመጠቀም መብት በዋስትና ሊያዝ የሚችልበት ጊዜ ከ25 አመት አይበልጥም፡፡ (19(5) | በሊዝ የተከራየ ባለሀብት የመጠቀም መብቱን በዋስትና ለማስያዝ ይችላል፡፡ (15(15) | • መሬት በሊዝ የተከራየ የመጠቀም መብቱን በዋስትና ያስይዛል፡፡ (8(4)<br>• | • በሊዝ የተከራየ ባለሀብት የመጠቀም መብቱን በዋስትና ለማስያዝ ይችላል፡፡ (15(3) |
| 14 | መንግስታዊና | • መንግስታዊና | • መንግስታዊም ሆነ | • መንግስታዊና | • መንግስታዊና |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት መሬት የማግኘት መብት | መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የብዙሀን ማህበራትና የሃይማኖት ተቋማት ለገንዘብ ትርፍ እስካልሆነ ድረስ የአርሶ አደሮችን በመሬት የመጠቀም መብት በማይጻረር ሁኔታ የሚጠቀሙበት መሬት በይዞታ የማግኘት መብት አላቸው። (6(4) | መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት የገጠር መሬት የማግኘት መብት አላቸው። 5(3) | መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተቋማት ከማልማት አላማዎች ጋር እየታየ በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ይኖራቸዋል። 5(15) | መንግስታዊ ያልሆኑ እና የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተቋማት ይዞታና የመጠቀም መብት ጊዜ በደንብ ይወሰናል። (7(5) |
| 15 | የወንጀል ሀላፊነት ስለሚያስከትሉ ጉዳዮች | • ይህንን አዋጅ የጣሰ ወይም አፈጻጸሙን ያሰናከለ አግባብ ባለው የወንጀል ህግ ተጠያቂ ይሆናል (31(2) | ይህንን አዋጅ የጣሰ አግባብ ባለው ህግ መሰረት ይቀጣል። (27) | ይህንን አዋጅ ወይም አዋጁን ተከትለው የወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን የጣሰ አግባብ ባላቸው የወንጀል ህግ ተጠያቂ ይሆናል(16) | • ይህንን አዋጅ የጣሰ አግባብ ባለው የወንጀል ህግ መሰረት ይቀጣል። (29(1)<br>• ከዚህ በተጨማሪ የትግራይ ክልል ህግ 11 አይነት የወንጀል ተግባራትን በክልል ደረጃ የደነገገ ሲሆን፣ የወንጀል ክርክሩን አይቶ የሚወስነውም የተወሰኑትን የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት የተወሰኑትን ደግሞ ወረዳ ፍርድ ቤት እንደሚያያቸው ይደነግጋል። (29(2-4) |

ሰንጠረዡ በአጠቃላይ ዋና ዋና ጉዳዮችን በማነጻጸር ያስቀመጠ ሲሆን፣ መሰረታዊ በሆነ መልኩ ሁሉም የክልል ህጎች ተመሳሳይነት ያላቸው ቢሆንም፣ ልዩነቶችም ይስተዋላሉ። የሚከተሉት እንደማሳያ ሊቀርቡ ይችላሉ።

1. በአማራ ክልል አካለመጠን ያላደረሱ ልጆች መሬት የማግኘት መብት እንዳላቸው በግልጽ ያስቀመጠ ሲሆን፣ ሌሎቹ መሬት የመጠቀም መብት እንዳላቸው ያስቀምጣሉ። ይህ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ከቤተሰባቸው መሬት በውርስ ወይም በስጦታ የሚያገኙትን መሬት መጠቀም የመቻል እንጂ በቀጥታ ከመንግስት መሬት ይሰጣቸው እንደሆነ ግልጽ አይደለም።

2. በትግራይ ክልል ህግ የጎጆ መውጫ ወይም መኖሪያ 20 በ20 የሆነ ቦታ እንደሚሰጣቸው ያስቀምጣል፡፡ ተመሳሳይ አይነት ድንጋጌዎችን በሌሎች ህጎች አናገኝም፡፡
3. በኦሮሚያ ቋሚ የሆኑ ተክሎችን እንደማንጎ፣ ቡናና የመሳሰሉትን መሸጥ ይከለክላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከእነዚህ ተክሎች የሚገኙ ምርቶችንም በተመሳሳይ መሸጥ እንደማይችል ያመለክታል፡፡ ለመሸጥ የሚቻለው ከመሬቱ ከግማሽ ያልበለጠውን የያዘውን ምርትና ይህም ቢሆን ከሶስት አመት ሊበልጥ እንደማይችል ያመለክታል፡፡ አላማው በምርት ሽያጭ ስም መሬቱ ወደሌላ ሶስተኛ ወገኖች እንዳይተላለፍ ይመስላል፡፡ የምርት ሽያጬን በተመለከተ ከሶስት አመት በላይ አይቻልም የሚለው በዘላቂነት ምርቱን መሸጥ መሬቱን እንደመሸጥ ተደርጎ ስለሚወሰድ ነው፡፡ ይሁንና ከግማሽ መሬት በላይ ያለውን አይሸጥም ማለት ምን ማለት ነው? ትርጉም የሚኖረው ለአንድ ሰው መሸጥ አይችልም በሚል ነው፡፡ አለበለዚያ ለግሉ ሊጠቀምበት ይገባል ወደሚል ትርጉም መውሰድ ተገቢ አይደለም፡፡ ከዚህ የተነሳም ይመስላል፣ በፍርድ ቤት ውሳኔ ከይዞታው አይፈናቀልም በሚል ድንጋጌ የተቀመጠው፡፡ በንኡስ አንቀጽ 6 ያስቀመጠው ግልጽ እንደሚያደርገው ዋናው ነገር መሬቱ በተዘዋዋሪ እንዳይሸጥ መከልከል ነው፡፡ በንኡስ አንቀጽ 8ትም መኖሪያ ቤትን የገዛ በተመሳሳይ የገዛውን መኖሪያ እንዲያነሳ ይጠይቃል፡፡ ይሁንና በክልሉ በሚወጣ ደንብና መመሪያ የበለጠ ግልጽ ሊሆን ይችላል ብሎ መገመት ተገቢ ነው፡፡ ተመሳሳይ ድንጋጌ በሌሎች የክልል ህጎች አናገኝም፡፡ እርግጥ በትግራይ ክልል ህግ አንዳንድ መተከልና መነቀል የሌለባቸው ዛፎች እንዳሉ ያመለክታል፡፡ ከዚህ አንጻር በተወሰነ መልኩ መመሳሰል አለው፡፡ ይሁንና የትግራይ ህግ አላማው የመሬቱን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል የተቀመጠ ድንጋጌ ነው ማለት ይቻላል፡፡
4. የአማራ ክልል የገጠር መሬት ህግ የገጠር መሬት ባለይዞታ ከቤተሰቡ አባላት ውጪም ለሌላ ሰው በስጦታ ማስተላለፍ እንደሚችል ያመለክታል፡፡ ሌሎች ክልሎች ስጦታ መስጠት የሚቻለው ለቤተሰብ አባል ብቻ እንደሆነ ገድበው ያስቀምጣሉ፡፡
5. የአማራ ክልል ህግ የመሬት ይዞታን በኑዛዜ ለቤተሰብ አባል ላልሆነም ማስተላለፍ እንደሚችል ያመለክታል፡፡ ሳይናዘዝ ከሞተ ደግሞ ልጅ ከሌለው የተወሰነ ይዞታ ያላቸው ወላጆችም ሊወርሱ እንደሚችሉ ያመለክታል፡፡ ስለሆነም መሬቱ የባልና ሚስት የጋራ ቢሆንም፣ ባል ለምሳሌ በኑዛዜ የእሱን ድርሻ ለሌላ ሰው ሊናዘዝ

ይችላል ማለት ነው፡፡ ይህ መብት ላይ ያለው ገደብ በተዳር ጓደኛው ላይ ጉዳት የሚያደርስ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

6. በትግራይ ክልል ህግ በአንቀጽ 17(1) የገጠር መሬት ባለይዞታ ሲሞት በቅድሚያ ልጁ እንደሚወርስ፣ ልጅ ከሌለው ግን መሬት የሌለው ወላጁ እንደሚወርስ ይደነግጋል፡፡ በንኡስ ቁጥር 2 ደግሞ በዚህ አዋጅ መሰረት የሚወርስ ልጅ የሌለው ከሆነ የልጅ ልጅ እንደሚወርስ ይደነግጋል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች አንጻር ሟች ልጅ የሌለው ከሆነና ነገር ግን መሬት የሌለው ወላጅ በአንድ በኩል፣ የልጅ ልጅ በሌላ በኩል ቢኖረው ማን የቀዳሚ ወራሽ እንደሚሆን አሻሚነት ያለው ነው፡፡
7. በትግራይ የከተማ ነዋሪ የሆነ መሬት ሊወርስ እንደማይችል በግልጽ የደነገገ ሲሆን፣ በአማራ ክልል ግን የገጠር ኑሮአቸውን ለመደጎም ዝቅተኛ ገቢ የሚያስገኝ ስራ እየሰሩ በከተማ የሚቀመጡ ሰዎች እንደአርሶ አደር እንደሚቆጠሩ ያስቀምጣል፡፡
8. ኪራይን በተመለከተ የሚደረገው ስምምነት ወይም ውል በኦሮሚያ ዋጋ የሚኖረው በግብርናና የገጠር ልማት ቢሮ ሲመዘግብና ሲጸድቅ ብቻ ነው፡፡ አለበለዚያ በህግ ፊት ዋጋ የለውም፡፡ በደቡብም በተመሳሳይ የገጠር መሬት ባለይዞታ መሬቱን ማከራየት እንደሚችል ያስቀመጠ ሲሆን፣ ይሁንና ይህ ውል በሚመለከተው አካል መጽደቅና መመዝገብ እንደሚኖርበት ያስቀምጣል፡፡ ስለሆነም የሚደረጉ የመሬት ኪራይ ውሎች ጥብቅ ስርአት ሊከተሉ እንደሚገባ ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል በአማራ ክልል ህጋዊ እንዲሆን የሚጠይቀው መስፈርት በጽሁፍ መደረግ ብቻ ነው፡፡ ለዚያውም ከሶስት አመት ለሚበልጥ ኪራይ፡፡ እስከሶስት አመት ለሚደረግ ኪራይ ግን በጽሁፍ እንዲሆን ግዴታ አይጥልም፡፡ በክልሉ ህግ መሰረት አግባብ ባለው አካል ዘንድ መመዝገብ ብቻ ነው እንጂ የሚጠይቀው፣ አግባብ ያለው አካል ውሉን የማጽደቅ ስልጣን ወይም ካላጸደቀው ውል አይደለም ወደሚል ድምዳሜ የሚያመራ አይደለም፡፡ የትግራይ ክልል ህግ ውለታዎቹ እንደሚመዘገቡ ያስቀምጣል እንጂ ከዚህ ያለፈ የሚመለከታቸው አካላት የሚያጸድቁት ስለመሆኑ አያስቀምጥም፡፡ ይሁንና ውለታው በጽሁፍ ሊሆን ይገባው አይገባው በአዋጁ ላይ የተቀመጠ ነገር የለም፡፡ ወደፊት ደንብ ሲወጣ ዝርዝሩ እንደሚቀመጥ ይደነግጋል፡፡
9. በትግራይና በኦሮሚያ አርሶ አደር ሊያከራይ የሚችለው ከሚያርሰው ከግማሽ የማይበልጠውን ብቻ ነው፡፡ በሌሎቹ ክልሎች ግን እንዲህ አይነት ገደብ የለም፡፡

10.የመሬት ሽግሽግን በተመለከተ ሁሉም ክልሎች ከመስኖ ልማት ጋር በተያያዘ ሽግሽግ ሊኖር እንደሚችል በግልጽ ያስቀመጡ ሲሆን፣ በአማራ ክልል ግን በተለየ መልኩ 80 በመቶ ከተስማሙ ብቻና በእነሱ ላይ ብቻ ተግባራዊ የሚደረግ የመሬት ሽግሽግ እንደሚደረግ ያመለክታል፡፡

11.የትግራይ ክልል የመንግስት ገቢ እያላቸው መሬት መያዝ እንደማይችሉ የሚያመለክት ሲሆን፣ በደቡብ ግን ከዚህ በተለየ ባልየው የመንግስት ስራ ቢኖረውም ሴቶቹ በስማቸው መሬት እንደሚሰጣቸው ያመለክታል፡፡ የአማራና የኦሮሚያ ክልል ህጎች ይህንን በተመለከተ በግልጽ ያስቀመጡት ነገር የለም፡፡ ይሁንና አንድ ቤተሰብ እንደ ቤተሰብ አንደኛው በከተማ ኑሮ ቢኖር ሌላቸው መሬት ይዞ ሊኖር ይችላል ወይ የሚለው ሊያከራክር ይችላል፡፡

12.የትግራይ ክልል ከሌሎች በተለየ መልኩ አዳዲስ ከመሬት አጠቃቀም ጋር የተያያዙ የወንጀል ድንጋጌዎችን ይደነግጋል፡፡ በአጠቃላይ ቁጥራቸው 11 የሚሆኑ የወንጀል ተግባራትን የዘረዘረ ሲሆን፣ ጉዳዩን ለማየትም ለቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት እና ለወረዳ ፍርድ ቤት ከፋፍሎ እናያለን፡፡ ሌሎቹ ክልሎች ግን በአጠቃላይ ወደወንጀል ህጉ በማጣቀስ ብቻ ነው የሚጨርሱት፡፡

በዚህ ምዕራፍ በአራቱ ክልሎች የወጡ ህጎች መሠረታዊ ገፅታ ባጭሩ ለማሣየት የተሞከረ ሲሆን፣ በአራቱም ክልሎች የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ህግ መነሻ በማድረግ አርሶ አደሩ የመሬት ክርክር የሚያልፍባቸውን ሁኔታዎች ስንመለከት የሚከተለውን ሠንጠረዥ ያለውን ሁኔታ እናገኛለን፡፡

<u>የመሬት ክርክር የሚያልፍባቸው ሒደቶች</u>

| ተ.ቁ | የአማራ ክልል | የትግራይ ክልል | የደቡብ ክልል | የኦሮሚያ ክልል |
|---|---|---|---|---|
| 1 | በቅድሚያ በሽምግልና ታይቶ በእርቅ እንዲፈታ ጥረት ይደረጋል፡፡ | በስምምነት ወይም በሽማግሌ እንዲያልቅ ይሞከራል፡፡ | በቀበሌ መሬት አስተዳደር በኩል ለሽማግሌዎች ቀርቦ ይወስናል፡፡ | በቀበሌ አስተዳደር በኩል ለሽማግሌዎች ቀርቦ ይወሰናል፡፡ |
| 2 | ለመደበኛ ወረዳ ፍርድ ቤት ይቀርባል፡፡ | የቀበሌ መሬት አስተዳደር ኮሚቴ ውሣኔ | በሽማግሌ ውሣኔ ቅር የተሰኘ ይግባኝ ለወረዳ ፍርድ ቤት | በውሣኔው ያልተስማማ ክስ ለወረዳው ፍርድ ቤት ያቀርባል |
| 3 | በወረዳው ፍርድ ቤት ያልተስማማ ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀርባል፡፡ | ይግባኝ ለወረዳ ፍርድ ቤት ያቀርባል፡፡ | በወረዳው ፍርድ ቤት ያልተስማማ ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀርባል፡፡ | በወረዳ ፍርድ ቤት ውሣኔ ያልተስማማ ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ይቀርባል |
| 4 | | የቀበሌ ኮሚቴ ውሣኔ ከተሻሻለ ወይም ከተሻረ ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ይቀርባል፡፡ | በከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ካልተስማማ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይቀርባል፡፡ | የከፍተኛው ፍርድ ቤት የወረዳውን ውሣኔ ካሻሻለው ወይም ከለወጠው ይግባኝ ለፌዴራል ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት |
| 5 | | የከፍተኛው ፍርደ ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ለክልሉ ጠቅላይ | የክልሉ ጠቅላይ ፍርደ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ | የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሣኔ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት | ስህተት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት | መሠረታዊ የህግ ስህተቶች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት |
| 6 | | የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት | ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት | ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት |

# ***ምዕራፍ አራት***

## ***የፌደራሉንና የክልሉን የህገ ማዕቀፎች በማስፈፀም በኩል የሚታዩ ችግሮች የመፍትሔ ሀሳቦች***

*ክልሎች የፌደራል መንግስት በፌዴራል ህገ መንግስት በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ያወጣውን የመሬት አጠቃቀም ህግ መሠረት በማድረግ ያወጧችውን የህግ ማዕቀፎች የክልሎች ልዩ ባህሪ እና የትኩረት ማዕከል የሆኑ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ቸግሮች ምላሽ የሚሰጡባቸው የተለያያ ይዘት ያላቸው ድንጋጌዎች በማካተት የወጡ መሆኑን በምዕራፍ ሶስት በተደረገው አጭር ዳሰሳ ለማሣየት ተሞክሮዋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ በሁሉም ክልሎች የሚነሱ የመሬት ክርክሮች መነሻ በማድረግ የሚታዩትን መሠረታዊ ችግሮች የችግሮቹን መንስኤና የመፍትሔ ሀሳቦች ለውይይት መነሻ ይሆኑ ዘንድ ይቀርባሉ፡፡*

### *4.1* ***በአርሶ አደሮች መካከል መሬትን መነሻ ያደረጉ ክርክሮች በሚመለከት፣***

*አርሶ አደሩ የእርሻና የይዞታ መሬትን መነሻ በማድረግ ጉዳዩን በመጀመሪያ አይተው ለመወሰን ስልጣን ላላቸው የቀበሌ አስተዳደር አካላት ወይም ለወረዳ ፍርድ ቤት የሚቀርቡ*

ጉዳዩች ብዛት ያላቸው ስለመሆናቸው በየወቅቱ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በኩል የሚቀርቡ ሪፖርቶች ያሳያሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በክልሎች የመሬት ክርክርን ለመፍታት ታስበው የተቀመጡ እስከ አምስት ደረጃ የሚደርሡ የመጀመሪያ ደረጃ ክርክር፣ ይግባኝና የክልል ሰበር ሥርዓት በማለፍ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት የሚቀርቡ ጉዳዩች ቁጥር ከዓመት ዓመት እየቀነሰ ሣይሆን እየጨመረ መሆኑን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መረጃ ያረጋግጣል፡፡

ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የእርሻ መሬትና ይዞት ክርክርን በሚመለከት የክልል ፍርድ ቤቶች መሠረታዊ የህግ ስህተት ፈፅመዋል በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት በአርሶ አደሮች የቀረቡ አቤቱታዎች፣

- 1998 ዓ.ም በ470 የሰበር መዛግብት፣
- በ1999 ዓ.ም በ842 የሰበር መዛግብት፣
- በ2000 ዓ.ም 941 የሰበር መዛግብት፣
- በ2001 ዓ.ም በ849 የሰበር መዛግብት፣
- 2002 ዓ.ም እስከ ህዳር 30 ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ብዙ በ413 የሰበር መዛግብት፣

የቀረቡ መሆኑን የጠቅላይ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድጅታል ዳታ ቤዝ መረጃ ያሣያል፡፡

ሁሉም መዛግብት በመመርመር ለክርክሩ መነሻ የሆኑትን ክርክሮች ለማጠቃለል የማይቻል ቢሆንም ከኦሮሚያ፣ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች፣ ከአማራና ከትግራይ ክልል የመጡ መዛግብትን በናሙናነት በመውሰድ ሲመረመሩ ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ጉዳዩች የሚከተሉትን ነጥቦች መሠረታዊ ጭብጥ ያደረጉ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

- የመሬት ባለይዞታነትን በአጥጋቢ ማስረጃ በማጣራት ውሣኔ ከመስጠት አንፃር የሚነሱ ችግሮችና ክርክሮች፣
- ሀሰተኛ የመሬት ባለይዞታ ማረጋገጫ ሰነዶችን መነሻ በማድረግ የሚነሡ ችግሮችና ክርክሮች፣
- የእርሻ መሬት የውርስ አወራረስና በስጦታ ማስተላለፍን አስመልክቶ የሚነሡ ችግሮችን ክርክሮች፣

- ባልና ሚስት መካለል ያለው ጋብቻ በፍች እንዲፈርሱ የሚሰጡ ውሣኔዎችን ተከትሎ የሚነሡ ችግሮችና ክርክሮች፣
- በመሬት የመጠቀም መብት ቀሪ የሚሆንባቸውን ሁኔታዎች መነሻ በማድረግ የሚነሡ ችግሮችና ክርክሮች፣
- አካለ መጠን ያልደረሡ ህፃናት በሞግዚት የመሬት ባለይዞታ የመሆን መብትና መሬትን የመጠቀም መብት መነሻ በማድረግ የሚቀርቡ ክርክሮች፣
- የፍትሐብሔር ህጉን ወይም የክልሉን የህግ ማዕቀፍ አተረጓጎም መነሻ የሚያደርጉ ክርክሮች፣
- በክርክር አካሄድ በቀበሌ ውስጥም ወረዳ ፍርድ ቤት ወይም ክልሎች የክልል ፍርድ ቤቶች ተፈፀሙ የሚባል መሠረታዊ ሥነ ሥርዓት ስህተት መነሻ በማድረጉና የሚቀርቡ ክርክሮች፣
- የመሬት ሽግሽግ አፈፃፀምን መነሻ ያደረጉ ክርክሮች፣
- የመሬት ኪራይ ሰበብ የሚፈፀም የእርሻመሬት ሽያጭ መነሻ ያደረጉ ክርክሮች፣
- ሥልጣን ባለው የማህበራዊ ፍርድ ቤት ወይም ፍርድ ቤት የተሰጡ ውሣኔዎችን ባለመቀበል ወይም ለማስፈፀም ምክንያት የሚቀርቡ ክርክሮች እና ሌሎች የአፈፃፀም እና የህግ አተረጓጎም የክርክር አሠራር ሥርዓቶችን መነሻ ያደረጉ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

## 4.2 የችግሮች መገለጫ እና መንስኤዎች

ከላይ በጥቅል ያሰቀመጥናቸው ለክርክር መነሻ የሚሆኑ ችግሮች በውስጣቸው በርካታ የመረጃ አያያዝ ጉድለትን፣ የክርክር አመራር ብቃትና ዕውነትን በማፈላለግ በኩል በአስተዳዳር አካላትና በፍትህ አካላት በኩል የሚታዩ ድክመቶችን፣ በህጎቹ ይዘትና ህጎቹ አተረጓጎም ሂደት የሚታዩ ድክመቶችንና ሌሎች የአሠራር ችግሮችን የሚያካትቱ ናቸው፡፡ ስለሆነም የችግሮቹ መገለጫና ገፅታ መረዳት መፍትሔዎቹን ለማፈላለግ ለምናደርገው ጥረት አስፈላጊ በመሆኑ በሚከተሉ መንገድ ዋና ዋናዎቹን ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

### 4.2..1. የመሬቱን ዕውነተኛ ባለይዞታ አጣርቶ ያለመወሰን

ከቀበሌ ጀምረው በክልሉ ጉዳዩን ለማየትና ለመወሰን የሚችሉ ፍርድቤቶችን አልፈው በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንባቸውን እያፈሰሱ የሚከራከሩ አርሶ አደሮች በቀዳሚነት የሚያነሡት ዋናው ችግር ክርክር የተነሳበት የእርሻ መሬት እውነተኛ ባለይዞታ ማን ነው? የሚለውን ጭብጥ በእውነተኛና አጥጋቢ ማስረጃ በማጣራት ውሣኔ አልተሰጠም የሚል ነው፡፡ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚቀርቡ የሰበር አቤቱታዎች አብዛኛዎች የሚዘጉት አርሶ አደሮች ክርክር የሚያቀርቡበት ጉዳይ የህግ ክርክር ሣይሆን የፍሬ ጉዳይ ክርክር ነው የሚል ነው፡፡

በዚህም ዋናው ምክንያት በአገሪቱ የተለያየ ክፍል በአርሶአደሩ መካከል የተደረገው የመሬት ድልድል በተለያየ ጊዜ የተደረገ መረጃዎች ተመዝግበው ያልተያዙና የማይገኙ መሆናቸው ነው፡፡ ስለሆነም አንድ አርሶአደር ሌላ ሰው ይዞታየን በሀይል ይዞብኛል፤ ድንበር ተጋፍቷል የሚለውን ክስ ለማስረዳት የሚቀርበው ማስረጃም ሆነ ክሱን ለመከላከል የሚቀርበው ማስረጃ የሰው ምስክር በመሆኑ እውነቱን በማፈላለግ በኩል ከፍተኛ ችግር ይከሰታል፡፡ ከዚህ አንፃር፣

- የመሬት ድልድል ከሽግግር ወቅት በፊትና በሽግግር ወቅት በተደረገባቸው የትግራይ የአማራ ክልል የተለያዩ ዞኖች የመሬት ድልድል ኮሚቴው መሬቱን የሰጠው ለማን ነው? በሚለው ጭብጥ ዙሪያ በወቅቱ የመሬት ደልዳይ ኮሚቴ አባል ነን የሚሉ ሰዎች ግማሾቹ የከሳሽ ምስክር በመሆን የሚመሠክሩ ሲሆን ግማሾቹ ለተከሳሽ የመከላከያ ምስክር በመሆን የሚመሠክሩ ሲሆን፣ ከዚህ አንጻርም በወቅቱ የመሬት ድልድል ኮሚቴ አባላት የነበሩ እነማን ናቸው ፣ ፣ የእርሻ መሬት በትክክል ለማንኛውም ተከራካራ/ለከሳሽ መይም ተከሳሽ/ የተሰጠና ማንኛው የምርት ሥራ ከመቼ ጀምሮ ሲሰራ እንደቆየ ለሚሉት በአግባቡ በማጣራት ሳይሆን የምስክሮችን ቃል በማበላለጥ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑ፣
- መሬቱን ተከሳሽ ከከሳሽ ምርት አምርቶ ለማከፋፈል ባደረገው ስምምነት የያዘው ስለመሆኑ ወይም በወኪልነት፣ በሞግዚትነት ይዞ የቆየ ስለመሆኑና ሌሎች ፍሬ ጉዳዩች በአግባብ በማጣራት ሳይሆን የምስክሮች ቃል በማበላለጥ ውሣኔ የሚሰጥ በመሆኑ፡፡

- የመሬት ድልድልና ሽግሽግ ለመጨረሻ ጊዜ በደርግ ጊዜ በተደረገባቸው የኦሮሚያ ክልል የደቡብ ክልልና ሌሎች አካባቢዎች አርሶ አደሮች መሬቱን ለእነርሱ በድልድል የተሰጣቸውና የእነርሱን ይዞታ የነበረ ስለመሆኑ በደርግ ጊዜ የቀበሌ ገበሬ ማህበር ሊቀ መንበር፣ ፀሐፊ ወይም የሸንጎ አካል ነበርን የሚሉ ሰዎች በምስክርነት እና በመከላከያ ምስክርነት የሚያቀርቡ መሆናቸውን በመጀመሪያ ሰዎቹ በወቅቱ የቀበሌ ባለሥልጣን የነበሩ መሆናቸውን፣ ከዚያም መሬቱ የማን ይዞታ እንደሆነ፣ በምን ምክንያት በተከሳሽ ይዞታ ስር እንደገባ፣ ከመቼ ጀምሮ ተከሳሽ እንደያዘው እና ሌሎች ዕውነቱን ለማወቅ የሚረዱ ፍሬ ጉዳዮችን ተጣርቶ ሣይሆን የምስክሮቹን ቃል በማበላለጥ ውሣኔ የሚሰጥ መሆኑ፣
- በርካታ አርሶ አደሮች የእርሻ መሬት ይዞታን ለማረጋገጥ የፍትሐብሔር ክስ ከማቅረባቸው በፊት በመጀመሪያ ተከሳሽ በይዞታ ላይ ሁከት ፈጥሮብኛል የሚል የወንጀል ክስ ለማህበራዊ ፍርድ ቤት በማቅረብና ምስክር አስመስክረው ጉዳዩን በደንብ ሣይጣራ ተከሳሹን ካስቀጡ በኋላ በዚህ በወንጀል ፍርድና ቅጣት መነሻ ተከሳሹ የያዘውን የእርሻ ማሣ ለማስለቀቅ የሚወሰዱ እርምጃዎችና የሚሰጡ ውሣኔዎች በመኖራቸው እና ሌሎች ፍሬጉዳዮች በማጣራት በኩል የሚያጋጥሙ የማስረጃ ችግር ምክንያት ዕውነት ላይ ለመድረስና አጣርቶ የመወሰን ችግር ምክንያት ክርክሮች ከአንደኛው እርከን ወደ ሌላው እየተሸጋገሩ እና እየተጓተቱ የሚሄዱ መሆኑን ለመገንዘብ ይችላል፡፡

በሌላ በኩል የመሬት ይዞታ መመዝገብና የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር መስጠት በተጀመረባቸው ክልሎች በአንድ የእርሻ መሬት ላይ የተለያዩና ተቃራኒ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የሚሰጥ መሆኑ፡-

- የቀበሌ የመሬት አስተዳዳር ኮሚቴ የአንደኛው አርሶ አደር ይዞታ እንደሆነ የፅሑፍ ማስረጃ ሲሰጥ፣ የወረዳ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ዴስክ ክርክር የተነሣበት መሬት የሌላኛው አርሶ አደር መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ የሚሰጥ መሆኑ እና ሀሰተኛ ማስረጃዎች ተፅፈው የሚቀርቡ መሆኑ፣
- የእርሻ ክርክር ለያዘው ፍርድ ቤት የቀበሌ መሬት አስተዳዳር ኮሚቴ ወይም የወረዳ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ዴስክ ሁለት ተቃራኒ የፅሑፍ ማስረጃዎችን

የሚሰጡበት ሁኔታ መኖሩ ፍሬጉዳዩን በማጣራትና እውነቱን በመረዳት ውሣኔ በሚሰጡት በኩል ለሚከሰቱ ችግሮች አይነተኛ ምክንያት ሆኖ ይገኛል፡፡

### 4.2.2 ውርስና ስጦታን የሚመለከቱ ችግሮች

- የእርሻ መሬት ውርስ አስመልክቶ ክልሎች ያወጡት የእርሻ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጆች የተለያየ ይዘት ያላቸው ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻር የእርሻ መሬት የመጠቀም መብት በውርስ የማስተላለፍ መብትና በእርሻ መሬት ላይ ያሉ ንብረቶች የመውረስ መብት አንድና ተመሣሣይ አድርጐ በማየት የመወሰን፣
- የፍትሐብሔር ህጉ የውርስ ህግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት የላቸውም በማለት በግልፅ በተደነገገበት ትግራይ ክልል ጭምር የእርሻ መሬትን ውርስ በፍታብሔር ድንጋጌዎች አንፃር አይቶ የመወሰን ሁኔታ መኖሩና፣
- ስጦታን በተመለከተ በስውርና ህገ ወጥ በሆነ መንገድ መሬቱን ለመሸጥ ለመጠቀም የሚሞክሩ ሰዎች ያሉ መሆኑና የስጦታ ውሉ በቀበሌ አስተዳደር ወይም በወረዳ ዲስክ የሚፀድቅበትና የሚመዘገብበት ሁኔታ መኖሩን በዚህ ምክንያት ክርክር ሲነሣ እውነቱ ሣይጣራና ህጉ ሣይገናዘብ የሚሰጡ ውሣኔዎች መኖራቸው፣

በሌላ በኩል መሬት በውርስ ወይም በስጦታ አግኝቻለሁ በማለት የሚች አርሶ አደር ህፃናት ልጆች፣ ሚስት፣ ተጧሪ አያትና አባት ይዞታውን እንዲለቁ የሚቀርቡ ክሶች የሚስተናገዱና አልፎ አልፎ ህፃናቱ የመሬት ይዞታ እንዲያስረክቡ የማስገደድ ውሣኔዎች የሚሰጡ በመሆኑ በዚህ በኩል እየተራዘሙ የመጡ ክርክሮችን በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

### 4.2.3 የሌሎች ችግሮች መገለጫና ገፅታ

- ባልና ሚስት ከመጋባታቸው በፊት በየአካባቢያቸው የያዙት የእርሻ መሬት ያላቸው ሆኖ እያለ ባል ወይም ሚስት ለብቻ በኖሩበት አካባቢ ያለው ተጋቢ ያለውን የይዞታ መሬት የመጠቀም መብት እንዲካፈል የሚቀርብ ክስና የሚደረግ ክርክር በዚህ ረገድ የሚሰጥ ውሣኔ ያለ መሆኑ፣ በተለይም በመሬቱ ላይ ያለውን ሀብት /ሰብል ተክል ወይም ዛፍ/ እና መኖሪያ ቤት የመካፈል መብትና በይዞታ መሬት የመጠቀም መብት

ተለይተው የማይወስኑ መሆኑ፣ ባል ሚስት ከማግባቱ በፊት ይዞት የነበረው የእርሻ መሬት፣ ሚስት ባል ከማግባቷ በፊት ይዛው የነበረው የእርሻ መሬት በፊት የእርሻ መሬት አብሮ ለሚኖረው ለሌላኛው ተጋቢ መሬቱን የመጠቀም መብት የማካፈል ግዴታ አለበት ወይስ የለበትም? በመሬቱ ላይ ያለውን ንብረት /መኖሪያ ቤት ሰብል ተክልና ዛፍ/ የመካፈል መብትና የመሬት ይዞታን የመጠቀም መብት የሚለው ላይ የህግ ማዕቀፎቹ ግልፅ አለመሆኑና በውሣኔ አሰጣጥ ሂደትም የሚታዩ ችግሮች፣

- የእርሻ መሬት የመጠቀም መብት ቀሪ የሚሆነው አንድ ሰው ያለ በቂ ምክንያት በራሱ ፈቃድ አካባቢውን መሬቱን ለቅቆ ሁለት ዓመትና ከዚያ በላይ ከሄደ መሆኑ በየህጎቹ ተገልጿል፡፡ አንድ አርሶ አደር መሬቱን ከሁለት ዓመት በላይ ከለቀቀ መንግስት መሬት ለሌላቸው አርሶ አደሮች በመሬት ሽግሽግ እንደሚሰጥ የፌዴራል እና የክልል የህግ ማዕቀፎች የሚደነግጉ ቢሆንም ይህ ጉዳይ ከይርጋ ድንጋጌዎች ጋር አንድና ተመሣሣይ ተደርጐ የሚጠቀስና የሚተረጉም ውሣኔ የሚሰጥ መሆኑ፣

- ከእርሻ መሬት የመጠቀም መብት ጋር በተያያዘ መንገድ በፍታብሔር ህጉ ስለ ይዞታ፣ ስለ ውርስ እና ስጦታ ውል የተደነገጉ ድንጋጌዎች የጉዳዩን ልዩ ባህሪ ባላገናዘበ ሁኔታ የሚተረጎሙ መሆኑ፣

- በቀበሌ ውሣኔ እንዲሰጡ ስልጣን የተሰጣቸው አካላት ለተከራካሪዎች መጥሪያ ሳይደርስ፣ የመከላከያ ማስረጃ ሣያቀርቡ፣ እውነቱን ሣያጣሩ የሚወስኑ መሆናቸውና በፍርድ ቤቶች በክርክር ሂደት የሚፈፀሙ የሥነ ስርአት ጥሰቶች ያሉ መሆናቸው፣

- የመሬት ሽግሽግ ይዞታው የተሰጠው ለእኔ ነው ለእኔ ነው በሚል ምክንያት የሚከራከሩ ሰዎችን መብት በማስረጃ አጣርቶ በመወሰን በኩል መረጃዎች በአግባቡ የማይያዙና ተጣርተው የማይወሰኑ መሆናቸው፣

- በመሬት ኪራይ ሰበብ የእርሻ መሬት ሽያጭ የሚፈፀምበት፣ በእርሻ መሬት ላይ ቤት የሚሠራበት፣ የኪራይ ውሉም ከመሬት አስተዳደርና አጠቃቀምን በተመለከተ ያወጡትን የህግ ማዕቀፎች በሚፃረር ሁኔታ ያለሚስት ወይም ያለ ባል ፈቃድ

የማከራየትና ከዚህ ጋር ተያይዘው በሚቀርቡ ክርክሮች ውሳኔ አሰጣጥ ችግሮች ያሉ መሆኑ፣

- አንዳንድ አካባቢ ከዚህ በፊት በውሣኔ ያለቁ ጉዳዮች ባለመቀበል ወይም የተሰጡ ውሣኔዎች በአግባቡ ባለመፈፀማቸው ምክንያት የሚቀርቡ ክርክሮች በአግባቡ እልባት የማያገኙ መሆናቸው

የመሬት አጠቃቀም መብት አስመልክቶ የሚነሱ ችግሮች መገለጫና ዋና ዋና ገፅታዎች እንደሆነ ለማየት ይቻላል፡፡

## 4.3. የመፍትሔ ሀሳቦችና ማጠቃለያ

የእርሻ መሬት ይዞታን መነሻ በማድረግ በሚደረጉ ክርክሮች የሚከሰቱ ችግሮች መግለጫ ከላይ የተገለፀው ሲሆን፣ ችግሮቹ ከእርሻ መሬት ይዞታና ተጠቃሚነት ጋር ህይወቱ ጥብቅ ቁርኝት ያለው አርሶ አደር ከፊል አርብቶ አደር እና አርብቶ አደር ህይወት ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ ያላቸው ናቸው፡፡ ስለሆነም ችግሮቹን ለመቅረፍ፡-

- እውነተኛው ባለይዞታ ማን ነው የሚለው ፍሬ ጉዳይ በቀበሌ መሬት አስተዳደር ኮሚቴ ወይም በሽማግሌ በፍሬ ጉዳይ ደረጃ ጊዜ ሰጥተው አጣርተው የሚወስኑበት ሁኔታ ያለ ቢሆንም አልፎ አልፎ የሚፈጠሩ ችግሮች ያሉ በመሆኑ ፍሬ ጉዳዩን በይግባኝ ደረጃ በማጣራት በመጀመሪያ ደረጃ ክርክር ወቅት ፍርድ ቤቱ ወይም ምትክ ዳኛ በማሰየም ደጋፊ የፅሑፍ ማስረጃዎች በማየትና በመመርመር በመመዘን በመወሰን ብዙዎቹን ችግሮች ለመቅረፍ ጥረት ማድረግ ይገባል፡፡

- የመሬት ክርክር አርሶ አደሩ በቂ መጥሪያ ሣይደርሰው፣ መከላከያ ማስረጃ ሣያቀርብ ቴክኒካል የሆኑ የሥነ ሥርዓት ጉዳዮችን መሠረት በማድረግ የሚሰጡ ውሣኔዎች አርሶ አደሩን ከመሬቱ የማፈናቀል ውጤት የሚያስከትል በመሆኑ ለጉዳዩ ትኩረት መስጠትና አርሶ አደር በሌለበት የሚታይ ጉዳይም ቢሆን እውነቱን ለማጣራትና ለመወሰን ተገቢውን ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

- የየክልሎቹ የህግ ማዕቀፎች መሠረታዊ መርሆች ልዩ ባህሪና ይዘት በመረዳት የህጎቹን ግብና ዓላማ መሠረት በማድረግ ህጎቹን መተርጎምና በተለይም ግለሰብ መቃወሚያ የማያደርጋቸው ጉዳዮች ይርጋ ህግ ጋር በማቀላቀልና ሌሎቹንም የህግ አተረጓጎም ግድፈቶችን በማረምና ለውሣኔ መሠረት የሆኑ የፌዴራልና የክልል የህግ ማዕቀፎች ድንጋጌዎችና ይዞታቸውን በማጣቀስ ውሳኔ መስጠት ይገባል፡፡

- ለፍርድ ቤት የሚላኩ የፅሑፍ ማስረጃዎች እና ሰነዶች ትክክለኛነት ማጣራት ተቃራኒ ማስረጃዎች ከመንግስት አካላት ሲልኩ ዕውነቱን ለማወቅና ለማጣራት የሚያስችሉ የተለያዩ የማጣሪያ መንገዶች መጠቀምና አጣርቶ መወሰን፣
- በአስተዳደር አካላት በኩል መረጃዎች በአግባቡ እንዲያዙ እንዲጠበቁ የማድረግ አስፈላጊነትን በተመለከተም በአንድ ወይም በሌላ መልኩ በሚዘጋጁ ፕሮግራሞች ግንዛቤው እንዲያዝና አሰራሩ እንዲዘረጋና እንዲለመድ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
- በየአካባቢው የሚታዩ ችግሮችን መነሻ በማድረግ በማጥናትና በማጠቃለል የጥናት ውጤቶችን ከመፍትሄ ሀሳቦች ጋር ማሳወቅ ያስፈልጋል፡፡
- በየአካባቢው ወጥተው ሥራ ላይ ስለዋሉ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ህጎች ደንቦችና መመሪያዎች አርሶ አደሩ መብቱንና ግዴታውን እንዲረዳ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ የገጠር የእርሻ መሬት በነፃ የማግኘት መብት፣ ከእርሻ መሬት ያለመፈናቀል መብት እና መሬቱን የመጠቀም መብት ህገ መንግስታዊ ጥበቃ እና ዋስትና የተሰጠው መብት ነው፡፡ አንድ አርሶ አደር በተለያየ ምክንያት አላግባብ ይህ መብቱን ካጣ የእሱና የቤተሰቡ የመኖር ዋስትው አደጋ ላይ የሚወድቅ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር ማንኛቸውም አርሶ አደር ጉዳዩ በአግባቡ ባለማጣራቱ ምክንያት ከሚደርስበት የፍትህ እጦት እና እሱና ቤተሰቡ የኑሯቸው ህልውና እንዳይናጋ ለማድረግ በሙያችን ዕውነቱን ለማውጣት እና ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት አስፈላጊውን ጥረትና ትጋት ማድረግ ያስፈልገናል፡፡